Wisdom at the source of the Blue Nile

እውነትን መፈለግና ስሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

# ናይል
# THE NILE



ኢ-ሜይል፡- bduinfo63@gmail.com or gracetsegi@gmail.com ድረ-ገጽ፡- http://www.bdu.edu.et የፌስቡክ ገጽ፡- www.facebook.com/bduethiopia

ናይል 4ኛ ዓመት፣ ቁጥር 6፣ ሕዳር 2009

## ያልተማከለ አስተዳደር በራዕይ ፐበብ 2017

በባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)

About Chinese Tests - HSK Exam
Dr. Zhang Wenxia

ለበላይ አካላት
ደስታ ተከስተ

ፍናፍንት ምእራፍ ሁለት
ታምሩ ከፈለኝ (የሻረግ)

ከጎዳናው በፊት
ቤተልሄም ሃይለማርያም

የአስመራ መንገድ
ቤተልሄም ሃብቴ(ባርካት)

## ፕሮፌሰር ረዳ ዳርጌ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ልምዳቸውን አካፈሉ

በአምሳሉ ጥላሁን

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቦርድ ጥቅምት 28/2009 ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ የትምህርትና ስነ-ባህሪ ኮሌጅ መምህርና ተመራማሪ ለሆኑት ለፕሮፌሰር ረዳ ዳርጌ በትምህርት ሳይኮሎጂ የሙሉ ፕሮፌሰርነት ማዕረግ ሰጠ፡፡ የኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚዩኒኬሽን ምክትል ፕሬዝደንት ጽ/ቤት የእንኳን ደስ አለዎት እና የፕሮፌሰርነት ህዝበ ገለጻ ስነ ስርዓት ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ እንዲያካፍሉ አድርጓል፡፡

በመርኃ ግብሩ ላይ የእንኳን ደስ አለዎት ንግግር ያደረጉት የጽ/ቤቱ ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 ዓ.ም አፍሪካ ውስጥ ካሉ አስር ምርጥ የምርምር

ገጽ 4



## የሕክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ የህክምና ዶክተሮችን አስመረቀ

በአምሳሉ ጥላሁን



የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ ለስድስት ዓመታት ትምህርታቸውን ሲከታተሉ የቆዩ የህክምና ዶክተሮችን አስመረቀ፡፡

በምረቃ ሥነ ስርዓቱ ላይ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የኮሌጁ ም/ዲን አቶ ባየህ አበበ የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በ2000 ዓ.ም ጀምሮ የህክምና ዶክትሬት ተማሪዎችን በመቀበል ማስተማር እንደጀመረ እና ኮሌጁ አሁን ለአራተኛ ጊዜ ወንድ 53፣ ሴት 12 በድምሩ 65 የህክምና ዶክተሮችን እንዳስመረቀ ገልፀዋል፡፡ ኮሌጁ በአሁኑ ሰዓት በአጠቃላይ 26 የትምህርት ዘርፎችን በመክፈት በማስተማር ላይ እንደሆነ እና ዩኒቨርሲቲው ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ ባለበት በሁለተኛ እና በሶስተኛ ዲግሪ ላይ

ገጽ 4

“የታካሚዎቼን ደህንነት በመጠበቅና መልካም አርአያ በመሆን የምችለውን ሁሉ በመስራት ለዩኒቨርስቲው መልካም ስም ጉልህ አስተዋፅኦ አበረክታለሁ፡፡”

ዶ/ር አክብረት ስመረ ... ገጽ 8

እውነትን መፈለግና ስሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

ናይል
THE NILE

# Bahir Dar University

## Motto of Bahir Dar University

"Wisdom at the Source of the Blue Nile"

"ከዓባይ ጓዳ ጥበብ ሲቀዳ"

## Mission

The mission of Bahir Dar University is to contribute substantially to the nation and beyond through high quality education, research and community services.

## Vision

The vision of Bahir Dar University is to become one of the ten premier research universities in Africa by 2025.

### Core Values

- Quality
- Discourse
- Innovation
- Integrity
- Democratic culture
- Social responsibility


# ናይል ጋዜጣ

በኢንፎርሜሽንና ስትራቴጂክ ኮሚኒኬሽን ም/ፕሬዚዳንት ጽ/ቤት
የውስጥ ግንኙነትና ኮሚኒኬሽን ክፍል
የሚዘጋጅ ወርሃዊ ጋዜጣ



**የአማካሪ ቦርድ አባላት**

ዶ/ር ፍቅረሰላም ጋረድ
አቶ አብይ መንክር
አቶ እምቢያለ በየነ
ወ/ሮ ሰውነት አለሙ
አቶ በላይነህ ወርቁ
ዶ/ር አልማዝ ጊዜው
አቶ ቢሰማ ካሳ
ወ/ሮ መድኃኒት በላቸው
አቶ ቴዎድሮስ ካሳዬ

**ዋና አዘጋጅ፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ም/ዋና አዘጋጅ**
ሂሩት አድማሱ

**አርታኢዎች**
ሂሩት አድማሱ

**ግራፊክስና ሌይአውት፡-**
ፀጋነሽ ሙሉጌታ

**ዘጋቢዎች፡-**
ታድዬ አስማረ
አምሳሉ ጥላሁን
ትዕግስት ዳዊት
ሙሉጎጃም አንዷለም

**አምደኞች፡-**
ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
ዛን ዌን (ዶ/ር)
ደስታ ተከስተ
ታምሩ ከፈለኝ
ቤተልሄም ሃይለማርያም
ቤተልሄም ሀብቴ

**ፎቶ አንሺዎች፡-**
ታምራት አታላይ
ሙሉጌታ ዘለቀ

**የኮምፒውተር ጽሁፍ፡-**
የሻለም መንግስቴ
እስከዳር ይስማው

**ትራንስፖርት፡-**
ማናለ ኃይሌ

**መልእክተኞች፡-**
ንብረት ታፈረ
አለምነሽ ሙሉ
መልሸው አጥናፉ


ስልክ፡- +251 583206088
+251 583207023

## ርዕሰ-አንቀጽ

# ለተሻለ ለውጥ ተሳትፏችንን እናሳድግ!

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 ከአፍሪካ ከሚገኙ አስር ምርጥ የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን ራዕይ ሰንቆ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል፡፡ ይህንን ራዕይ ለማሳካት ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ይህንን ራዕይ በመሰነቅ የጀመረውን ጉዞ በሰው ሀይልና በግብአት ራሱን በማጠናከር ለስኬት በሚያደርገው ጉዞ የምሁራኑ፣ የተማሪው እና የአስተዳደር ሠራተኛው ያላሰለሰ ጥረት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል፡፡ ለዩኒቨርሲቲው ግቦች እና እቅዶች ስኬት የማህበረሰቡ የነቃ ተሳትፎ ወሳኝነት እንዳለው ይታወቃል፡፡

ምሁራን ወጣቱን የሰው ኃይል በእውቀትና በክህሎት በመደገፍ፣ የማህበረሰቡን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ የምርምር ሥራዎችን በመስራትና ወደ ተግባር በመለወጥ እንዲሁም ማህበረሰብ ተኮር የሆኑ አገልግሎቶችን በመስጠት ኃላፊነታቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡ የዩኒቨርሲቲው ምሁራን ያላቸውን እውቀትና ሀላፊነታቸውን በመወጣት በምርምርና በጥናት በመደገፍ ሳይንሳዊ ትንታኔዎችን በመስጠት ማህበረሰቡን የሚጠቅሙና የሚደግፉ ሥራዎችን መሥራት ይጠበቅባቸዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎችም የነገ ሀገር ተረካቢዎች በመሆናቸው ራሳቸውን በእውቀት፣ በክህሎትና በአመለካከት በመለወጥ ነገ የማህበረሰቡን ችግር ለመፍታት ለራሳቸው ቃል መግባት ይኖርባቸዋል፡፡ ለስኬት በሚያደርጉት ጉዞ የተለያዩ ወጣ ውረዶች እንደሚገጥማቸው በመረዳት ራሳቸውን ለለውጥ መዘጋጀት አለባቸው፡፡ በውጤታማነት መንገዳቸው ላይ ያሉትን እንቅፋቶችን እንደ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም የተለያዩ የመፍትሄ ሀሳቦችን በማመንጨትና የተሻለውን በመምረጥ እንዴት ማለፍ እንዳለባቸው በመማርና በመገንዘብ ሀገራቸው የምትጠብቅባቸውን ኃላፊነት ለመወጣት መጠንከር አለባቸው፡፡ የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች ሀገርን ለማልማት በሚደረገው የትውልድ ቅብብሎሽ ተቋሙ ያስታጠቃቸውን ዕውቀትና ክህሎት ከነባራዊ ሁኔታ ጋር በማገናዘብ የድርሻቸውን መወጣት ይኖርባቸዋል፡፡

ምሁራኑ መማር ማስተማሩን፣ ምርምሩን፣ የማህበረሰብ ተኮር አገልግሎቱን እንዲሁም የቴክኖሎጂ ሽግግሩን ለማጠናከር ደፋ ቀና ሲሉ እንዲሁም ተማሪዎች ከመምህራኖቻቸው የሚያገኙትን እና ለማግኘት የሚጥሩትን እውቀትና ክህሎት እንዴት ወደ ተግባር መቀየር እንዳለባቸው ሲጥሩ ከበስተጀርባ ደጀን በመሆን አስፈላጊውን አገልግሎት የሚሰጡት ደግሞ የአስተዳደር ሰራተኞች ናቸው፡፡ ራሳቸውን በየጊዜው በክህሎትና በእውቀት በማዳበር የማስፈፀም አቅማቸውን በማሳደግ የዩኒቨርሲቲውን ራዕይና ተልዕኮ ለማሳካት በሚደረገው ርብርብ የራሳቸውን ዕውቀት፣ ክህሎትና ጉልበት በመጠቀም የሚጠበቅባቸውን ኃላፊነት ሊወጣ ይገባል፡፡ የአስተዳደር ሠራተኞች የሚፈለግባቸውን የተለያዩ ተግባራት በእቅድ በመመራት በማከናወን መልካም አፈፃፀሞችን ማስመዝገብ የራዕይ ጥበብ 2017 ዋነኛው ማሳለጫ ነው፡፡ ዩኒቨርሲቲው ሀገሪቱ የምትፈልገውን በከፍተኛ ደረጃ የሰለጠነ የሰው ኃይል በማፍራት ለሀገር እድገትና ልማት የበኩሉን አስተዋፅኦ ለማበርከት በሚያደርገው ጥረት የአስተዳዳር ሠራተኛው ሚና ከፍተኛ ነው፡፡ ይህንን ሚና ወደ ተሻለ ደረጃ ለማሸጋገር የበለጠ መስራትና ለለውጥ መነሳት ያስፈልጋል፡፡

ምሁራን፣ ተማሪዎች እና አስተዳደር ሠራተኞች በሚያደርጉት የራዕይ ጥበብ 2017 የስኬት ጉዞ የሚገኙትን መልካም አጋጣሚዎች በመጠቀምና የሚያጋጥሙትን ክፍተቶች በመሙላት ለተሻለ ለውጥ በጋራ መሥራት አለባቸው፡፡ ይህንን እውን በማድረግ ረገድ የሁላችንም ተሳትፎ ወሳኝነት ስላለው ለበለጠ ለውጥ ተሳትፏችንን እናሳድግ!

## እውነትን መፈለግና ለሌላው ማሳወቅ ማህበራዊ ኃላፊነታችን ይሁን!

To follow the latest news about BDU, check out our website:
www.bdu.edu.et
facebook page:
www.facebook.com/bduethiopia

## ቁልፍ መልዕክት

# ያልተማከለ አስተዳደር በራዕይ ጥበብ 2017

ባይሌ ዳምጤ (ዶ/ር)
የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት

ፈጣንና ወጪ ቆጣቢ በሆነ መንገድ ስራን ከሚያሳልጡ ነገሮች አንዱ ያልተማከለ አስተዳደር ነው፡፡ ይህን ሀላፊነት ከተጠያቂነት ጋር በማቀናጀት የአንድን መስሪያ ቤት ወይም ሀገር አስተዳደር ስልጣን አንድ ቦታ እንዳይከማች በማድረግ ስራን የሚያቀላጥፍ አሠራር ነው፡፡ ይህ አጭር ጽሑፍ በራዕይ ጥበብ 2017 ያልተማከለ አስተዳዳር በመከተላችን ያገኘናቸው ውጤቶችና የገጠሙን ተግዳሮቶች በማቅረብ የዩኒቨርሲቲያችን ማህበረሰብ እንዲወያዩበትና ያልተማከለ አስተዳደር ያስከተለውን ተግዳሮቶች እንዲቀረፉ የሚያደርግ ሁኔታ እንዲፈጠር ለማድረግ ያለመ ነው፡፡

የዩኒቨርሲቲያችን የራዕይ ጥበብ 2017 መስመር ቀልጣፋ አስተዳደር ከማረጋገጥ አንፃር አንዱና ዋነኛ ትኩረት ያልተማከለ አስተዳደር በማረጋገጥ ሁሉም አገልግሎቶች በየጊቢዎቹና ፋካሊቲዎቹ እንዲሰጡ ማድረግን ያቀፈ ነው፡፡ በዚህም መሠረት በተለያዩ እርከኖች ያሉ ሀላፊዎችና የየጊቢዎች መሪዎችና መካከለኛ አመራሮች ወደርየለሽ በሚባል አኳያ የመወሰን ስልጣን እንዲያገኙ ተደርጓል፡፡ ዩኒቨርሲቲው ያልተማከለ አስተዳደርን ከጠንካራ የክትትልና የድጋፍ ስርዓት ጋር በማስተሳሰር እንዲተገበሩ በማድረግ ከፍተኛ ርብርብ አድርጓል፡፡

ያልተማከለ አስተዳደር በመከተላችን በርካታ የተማሪ አገልግሎችን በፍጥነት ለማሟላት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ በተጨማሪም መምህራን፣ ሠራተኞችና የውጭ ደንበኞች የተለያዩ አገልግሎቶችን (አበል ማወራረድ፣ ክፍያ መቀበል፣ ቅጥርና ሌሎች) በቅርብ እንዲያገኙ በማድረግ የተጠቃሚዎችን ጊዜ ከመቆጠባችንም በላይ እርካታቸውን ለማሳደግ ተችሏል፡፡ ቤተ-ሙከራዎች ማደራጀትን ጨምሮ በርካታ ለተልዕኳችን መሳካት የሚያግዙ ስራዎችን በፍጥነትና በጥራት እንድንሠራ እድል ሰጥቶናል፡፡

ከላይ የጠቀስናቸው ጥቅሞች እንደተጠበቁ ሆነው ያልተማከለ አስተዳደር ያስከተላቸው ተግዳሮቶችም አሉ፡፡ በአንድ በኩል በተሰጠው የሀላፊነት መጠን አለመወሰንና አለመተግበር ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ያልተማከለ አስተዳደርን እንዲሁ የመለቀቅና ለሚመለከታቸው ክፍሎችም ሪፖርት ማድረግን በሚገባ አለመተግበርና በራስ የቆመ ተቋም አይነት አድርጎ የመውሰድ ዝንባሌ መኖሩ የሚጠቀሱ ተግዳሮቶች ናቸው፡፡ ሌላው ተግዳሮት ያልተማከለ አስተዳደር የተሰጣቸው የተለያዩ ክፍሎች ዩኒቨርሲቲው የሚመድባቸውን የተለያዩ ግብአቶቸችና ነገሮች ‘ለኔ ይገባል ለኔ’ የሚል የጠበበ አመለካከት በመያዝ ትንሽ ነገርም ቢሆን ለማከፋፈል ከባድ መሆኑና የንትርክ ምንጭ ሆኖ ለማስማማት እያስቸገረ መምጣቱ ነው፡፡ እነዚህንና ተያያዥነት ያላቸውን ያልተማከለ አስተዳደርን መሰረት አድርገው የገጠሙንን ተግዳሮቶች የዩኒቨርሲቲያችን መምህራን፣ ሠራተኞችና ተማሪዎች ያለው አንድ ተቋም ብቻ መሆኑን በመረዳትና በዩኒቨርሲቲው ስር ያሉ ሁሉም ተቋሞች የተሰጣቸውን ሀላፊነት እስከ ተጠያቂነት ድረስ እንዲወጡ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራርም ጠንካራ የክትትልና ድጋፍ ስርዓት በመዘርጋት የተከሰቱትን መልካም ያልሆኑ ዝንባሌዎች ማረም ይኖርበታል፡፡ የተሰጠንን ሀላፊነት በሚገባና በዩኒቨርሲቲው አሠራርና አቅጣጫ መሰረት መተግበር የሁላችንም ግዴታ ነው፡፡

ራዕይ ጥበብ 2017ን እናሳካለን!

## የዋና አዘጋጇ መልዕክት

ውድ አንባቢዎቻችን

ናይል ጋዜጣ ‘ሀ‘ ብላ 2005 ዓ.ም መታተም ከጀመረች ወር አንስቶ እስካሁን ለአንባብያን ወቅታዊ የሆኑ መረጃዎችን እንዲሁም የተለያዩ አስተማሪና አዝናኝ የሆኑ ጹሁፎችን በማቅረብ እዚህ ደርሳለች፡፡ ጋዜጣችን ወርሃዊ ብትሆንም መረጃዎችን ሰፋ ባለ ሁኔታ በማቅረብ የዩኒቨርሲቲውን ገጽታ በመገንባት ረገድ ከፍተኛ ሚና እየተጫወተች ትገኛለች፡፡

በያዝነው 2009 ዓ.ም ዩኒቨርሲቲው የተመሰረተበትን በዓል ሲያከብር ናይል ጋዜጣም የተመሰረተችበትን 4ኛ ዓመት አስመልክቶ በተለያዩ ዝግጅቶች ተከብሮ ይውላል፡፡ ናይል ባሳለፍነው አራት አመታት ውስጥ ምንም እንኳን የተለያዩ ክፍተቶች ቢያጋጥሙም በተከታታይ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ መረጃ በመስጠት ቀዳሚ ናት፡፡ የዝግጅት ክፍላችንም ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲን በይበልጥ በማስተዋወቅና ወቅታዊ መረጃ በመስጠት ተመራጭ ለመሆን አስፈላጊውን ሁሉ እያደረገ ይገኛል፡፡

ውድ አንባቢዎቻችን - እናንተም በጋዜጣችን ላይ በመሳተፍ ከጎናችን እንድትሆኑ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፡፡

# አበይት ዜናዎች

## ማዕከሉ ዓለም አቀፍ የኢንተርፕርነርሽፕ ሳምንትን አስመልክቶ አውደ ጥናት አካሄደ

በሙሉጉጃም አንዱአለም

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የኢንተርፕርነርሽፕ ልማትና ማበልፀጊያ ማዕከል የዓለም አቀፍ የኢንተርፕርነርሽፕ ሳምንት አስመልክቶ የተለያዩ ዝግጅቶችን ያካተተ የአንድ ቀን ዓውደ- ጥናት በዩኒቨርሲቲው የመሰብሰቢያ አዳራሽ አካሄደ፡፡

የዩኒቨርሲቲው የእውቀትና ቴክኖሎጂ ሽግግር ዳይሬክተር ዶ/ር የሻምበል መኩሪያው ለተሳታፊዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈው ዩኒቨርሲቲው የሰነቀውን ራዕይ ከግብ ለማድረስ በርካታ አኩሪ ተግባራትን እያከናወነ ያለና በሀገራችን ውስጥ ካሉ ጠንካራ ዩኒቨርሲቲዎች ጐራ የሚመደብ ስለሆነ በኢንተርፕርነርሽፕ ዘርፍም ማዕከል በማቋቋም ልዩ ተሰጥኦና ፍላጐት ያላቸውን የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብም ሆነ የከተማው ነዋሪዎችን በተለያየ መንገድ ድጋፍና ክትትል እያደረገ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡

ዶ/ር የሻምበል አያይዘውም በአገራችን ውስጥ የሚገኙ አምስት ዩኒቨርሲቲዎች በኢንተርፕርነርሽፕ ድርሻቸውን ለመወጣት ማዕከል አቋቁመው ከመማር ማስተማር፣ ከምርምርና ከማህበረሰብ አገልግሎት ጐን ለጐን እያበረከቱት ያለው ሚና ወሳኝ ሲሆን ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲም ከእነዚህ ተርታ በመሰለፍ ለኢንተርፕርነርሽፕ ልዩ ትኩረት በመስጠት በእውቀትና ቴክኖሎጂ በማገዝ እንዲሁም መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ባለድርሻ አካላት ጋር በመወያየት ጉልህ አስተዋፅኦ እያበረከተ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

የኢንተርፕርነርሽፕ ልማትና ማበልፀጊያ ማዕከል ዳይሬክተር ወ/ሮ አለምፍሬ ደረሰ ማዕከሉ በቢዝነስና ኢኮኖሚክስ ኮሌጅ መምህራን ጠያቂነትና በዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራር ተነሳሽነት እንደተቋቋመና ዘርፈ ብዙ የሥራ ፈጠራ ተሰጥኦችን በመደገፍና በመከታተል በርካታ ሥራ እየሰራ መሆኑን ገልፀው የዓውደ ጥናቱ ዋና ዓላማ ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብና ከውጭ ለመጡ እንግዶች ስለኢንተርፕርነርሽፕ ምንነትና ጠቀሜታው እንዲሁም እንዴት ስራን መጀመር እንደሚቻል ግንዛቤ ለማስጨበጥ ታልሞ መሆኑን አስገንዝበዋል፡፡ ወ/ሮ አለምፍሬ አያይዘውም 23 ዓይነት የተለያዩ አዳዲስ የኢንተርፕርነርሽፕ ፈጠራዎች በተማሪዎች ለማዕከሉ ቀርበው ከነዚህ መካከል የካበተ ልምድ ባላቸው ሰዎች ተገምግመው

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## ተቋሙ ጉባዔ አካሄደ

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፔዳጎጂና ትምህርት ምርምር ተቋም በ2006 እና በ2007 ዓ.ም የሰራቸውን የምርምር ኘሮጀክቶች ለዩኒቨርስቲው ማህበረሰብ አቀረበ፡፡

በመርኃ ግብሩ ላይ የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የተቋሙ ዳይሬክተር ዶ/ር ዳዊት አስራት የፔዳጎጂና ትምህርት ምርምር ተቋም በባሕር ዳር ከተማና በዙሪያው ባሉ በተመረጡ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም በአገር አቀፍ ደረጃ በትምህርት ዙሪያ ምርምሮችን በማካሄድ ላይ እንደሚገኝ ገልጸው ከ2007 ዓ.ም ጀምሮ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት የጥራት ማረጋገጫ ተቋም ያወጣቸውን ነጥቦች በመከተል ችግር ፈች የሆኑ ምርምሮች ወይም ቅድመ ጥናቶች እያካሄደ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ በ2017 ዓ.ም አፍሪካ ውስጥ ከሚገኙ አስር የምርምር ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን ራዕይ ሰንቆ እየሰራ እንደሚገኝና ለዚህ ራዕይ ስኬት ዩኒቨርሲቲው ያቋቋማቸው ኘሮጀክቶች የምርምር ስራውን አጠናክረው ሲሰሩ እንደሆነ የገለጹት የዩኒቨርሲቲ የምርምር ዳይሬክተር ዶ/ር ዋሴ አንተነህ የምርምር ኘሮጀክቶች መከፈታቸው ብቻ ትርጉም እንደሌለውና ሁሉም የምርምር ማዕከላት የማህበረሰቡን ችግር ፈች የሆኑ ምርምሮችን መስራት እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል፡፡ መማር ማስተማር ከምርምር የተነጠለ እንዳልሆነና በተለይ የድህረ ምረቃ መምህራን እና ተማሪዎች ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጡት እንደሚገባ የተናገሩት ዶ/ር ዋሴ በዩኒቨርሲቲው የሚካሄዱ የምርምር ኘሮጀክቶች ምን ደረጃ እንደደረሱ ማየት አስፈላጊ በመሆኑ የፔዳጎጂና የትምህርት ምርምር ማዕከል በዚህ ረገድ በር ከፋች በመሆኑ ሊመሰገን እንደሚገባና ሌሎች የምርምር ማዕከላትም ልምድ ሊወሰዱ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

## የአካል ጉዳተኞች ቀን በዩኒቨርሲቲው ተከበረ

በሙሉጉጃም አንዱአለም

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ስርዓተ ፆታ ዳይሬክቶሬት አዘጋጅነት በዓለም አቀፍ ደረጃ ለ25ኛ እና በኢትዮጵያ ለ24ኛ ጊዜ እየተከበረ ያለውን የአካል ጉዳተኞች ቀን «ለመጭው ዘመን ብሩህነት አካለ ጉዳተኞችን በማካተት 17ቱን ዘላቂ የልማት ግቦች እናሳካለን!» በሚል መሪ ቃል በተለያዩ ዝግጅቶች ተከበረ፡፡

የትምህርትና ስነ-ባህሪ ሣይንስ ኮሌጅ ዲን ዶ/ር አንዳርጋቸው ሞገስ ለታዳሚዎች የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈው ለአካል ጉዳተኞች ልዩ ድጋፍና እንክብካቤ እንደሚያስፈልጋቸው ቢታወቅም የበለጠ ትኩረት ለመስጠት የበዓሉ መከበር ጉልህ ፋይዳ እንዳለው አስገንዝበዋል፡፡ አካል ጉዳተኞች እምቅ እውቀት እንዳላቸውና እንደማንኛውም ማህበረሰብ ሁሉንም የሥራ ዓይነት ማከናወን ስለሚችሉ የበዓሉ መከበር ዋና ዓላማ በራስ የመተማመን ወኔያቸውን ከፍ ለማድረግና ሁሉም የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ትኩረት እንዲሰጠው ታልሞ መዘጋጀቱን ዶ/ር አንዳርጋቸው በአፅንኦት ተናግረዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የስርዓተ ፆታ

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## ፕሮፌሰር ረዳ ዳርጌ...

ከገጽ 1 የዞረ

ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ ለመሆን ራዕይ ሰንቆ እየሰራ እንደሚገኝና ለራዕዩ ስኬት እንደ ፕሮፌሰር ረዳ ያሉ ተመራማሪዎችን ሚና ላቅ ያለ በመሆኑ መርኃ ግብሩ የተዘጋጀው ለፕሮፌሰር ረዳ እውቅና ለመስጠት እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የምርምር ዩኒቨርሲቲ እሆናለሁ ብሎ ሲነሳ የሁለተኛና የሶስተኛ ዲግሪ የትምህርት መርኃ ግብሮች ከግማሽ በላይ ማሳደግ እንዲሁም የመምህራን ማዕረግ ከግማሽ በላይ የሚሆኑት ከረዳት ፕሮፌሰርነት በላይ መሆን እንዳለበት የጠቆሙት ዶ/ር ፍቅረሰላም ከፕሮፌሰር ረዳ የስኬት ህይወት ብዙ እንማራለን ብለዋል፡፡

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የትምህርት የልህቀት ማዕከል በመሆኑ የሚሰራቸው የምርምር ሥራዎች በሙሉ በትምህርት ዙሪያ እንደሆኑ እና ዩኒቨርሲቲው የምርምር ዩኒቨርሲቲ ለመሆን እየሰራ በመሆኑ ለዚህ ራዕይ ስኬት እንዲሁም የማህበረሰቡን ችግር የሚፈቱ ፕሮጀክቶችን በመቅረፅ ለወደፊቱ ለመሥራት እቅድ እንዳላቸው የገለፁት ልምዳቸውን ለዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ ያካፈሉት ፕሮፌሰር ረዳ ናቸው፡፡ ፕሮፌሰር ረዳ የምርምር ሥራቸውን የጀመሩት ለመጀመሪያ ዲግሪያቸው የመመረቂያ ጽሁፍ በሚሰሩበት ወቅት እንደሆነ ገልፀው ነገር ግን እዚህ ደረጃ ላይ ለመድረስ ብዙ ውጣ ውረዶችን በማለፍ እንደሆነ ለተሳታፊዎች ምክር አዘል መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

በመርኃ ግብሩ ላይ የተገኙት የዩኒቨርሲቲው መምህራንና ተመራማሪዎች ለፕሮፌሰር ረዳ የእንኳን ደስ አለዎት መልዕክት ካስተላለፉ በኋላ የተሰጠው ማዕረግ ትልቅ ኃላፊነት ስለሆነ በመማር ማስተማሩና በምርምር ሥራው ትልቅ ልምድ ያላቸው ምሁር በመሆኑ ለወደፊቱ የማህበረሰቡን ችግር ሊፈቱ የሚችሉ ጥናትና ምርምሮች በማካሄድ ላይ ትልቅ ትኩረት በመስጠት ሊሰሩ እንደሚገባቸው ጠቁመዋል፡፡

## የሕክምናና ጤና ሳይንስ ...

ከገጽ 1 የዞረ

ኮሌጁ ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት እየሰራ እንደሆነ አቶ ባየህ ጠቁመዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ በበኩላቸው ለምረቃኑና ለተመራቂ ቤተሰቦች የእንኳን ደስ ያላችሁ መልዕክት ካስተላለፉ በኋላ ተመራቂ ተማሪዎች ተመረቅኩ ከሚለው ስሜት በስተጀርባ ሁልጊዜ አዲስ እውቀትን መፈለግ ላይ የተመሰረተ ህይወት እንዲመሩ አሳስበዋል፡፡ ተመራቂ ተማሪዎች ከዩኒቨርሲቲው ጋር ያላቸው ቁርኝት በማጠናከር ለዩኒቨርሲቲው አምባሳደር በመሆን እንደሚያገለግሉ ያላቸውን ተስፋ ተናግረዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የቦርድ አባልና የዕለቱ የክብር እንግዳ ዶ/ር አለማየሁ ዋሴ ሐኪሞች የማያቋርጥ የዕውቀት ጅረት ውስጥ ራሳቸውን መክተት እንዳለባቸውና ሁሌም ለመማር፣ ለማወቅ የሚተጉ በቅንነትና በትጋት ከማገልገል በላይ ጥልቅ ምርምር በማድረግ በሀገር በቀል ፈውስ ሀገር በቀል ህክምና መፍጠር እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል፡፡ የህክምናና ጤና ሳይንስ ትምህርት ከሰው ህይወት ጋር የተያያዘ በመሆኑ ተመራቂ ተማሪዎች በከፍተኛ የሙያ ብቃትና ስነ ምግባር ሕብረተሰቡን እንዲያገለግሉ ዶ/ር አለማየሁ አደራ ብለዋል፡፡

ከተመራቂዎች መካከል ከፍተኛ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች የወርቅ ሜዳልያ፣ የላፕቶፕና ታብሌት ኮምፒውተሮች ሽልማት ተበርክቶላቸዋል፡፡

## የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክት አፈፃፀም ጉብኝት ተደረገ

በታድዬ አሰማረ

በዩኒቨርሲቲው የምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚዳንት ዶ/ር ሙሉነሽ አበበ የተመራ የልዕካን ቡድን ዩኒቨርሲቲው የማህበረሰብ አገልግሎት ከሚሰጥባቸው በአቸፈር ወረዳ አብችክሊ እና አፋርፊዳ ቀበሌዎች ላይ በሞዴል አርሶ አደሮች የሚያካሄዱትን የሰርቶ ማሳያ ፕሮጀክቶችን ከወረዳው ኃላፊዎችና ባለሙያዎች ጋር በመሆን ጐብኝት አካሄደ፡፡

ዶ/ር ሙሉነሽ የሠርቶ ማሳያ ፕሮጀክቱን በጐበኙበት ወቅት ከሞዴል አርሶ አደሮችን ጋር ባደረጉት ውይይት እንደገለጹት ዩኒቨርሲቲው የ1.2 ሚሊዮን ብር ፕሮጀክት በመቅረፅ ከአርሶ አደሮች ጋር እየሰራ ያለው አርሶ አደሩ የጉልበቱና የላቡ ተጠቃሚ እንዲሆንና የተሻለ የህይወት አኗኗር እንዲኖረው ለማድረግ ነው፡ ፡ ፕሮጀክቱ የሁሉንም ገበሬዎች ህይወት ይቀይራል በማለት ሳይሆን የተመረጡት አርሶ አደሮች ሠርቶ ማሳያ (ሞዴል) በመሆን ሌሎች ገበሬዎች እነሱን በመከተል የቴክኖሎጂው ተጠቃሚ እንዲሆኑ ይፈለጋል ያሉት ዶ/ር ሙሉነሽ በሞዴል አርሶ አደሮች ያገኙትን የቴክኖሎጂ ሽግግር እውቀትና የኢኮኖሚ ለውጥ ለሌሎች በማስተላለፍ አርሶ አደሩ የኢኮኖሚ ባለቤት እንዲሆን ማድረግ እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል፡፡

ሞዴል አርሶ አደሮች እንደተናገሩት ዩኒቨርሲቲው ባደረገላቸው ድጋፍ በለጠ ድንች የተባለ የተሻሻለ የድንች ዘር እና ሮዳስ ሳር የተባለ የከብት መኖ የአካባቢው አርሶ አደሮች ተጠቃሚ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

ዩኒቨርሲቲው ከወረዳው ጋር በመተባበር በለጠ ድንች ዝርያ ላይ እና ከእንስሳት መኖ ደግሞ ሮዳስ ሳር ላይ ትኩረት በማድረግ የተገኘውን ምርጥ ተሞክሮ ለማስፋት እና በተለይ በአጭር ጊዜ ውስጥ የወረዳውን አርሶ አደር ለማድረስ እየሰራ ይገኛል፡፡ በተለይ ለአርሶ አደሩ እና ለሙያተኛው የአቅም ግምባታ ስልጠናዎችን በመስጠትና ለአርሶ አደሮች የግብይት አቅርቦት በመሸፈን ነው፡፡ የማሳ ዝግጅትን፣ የዘር አዘራርን፣ የተባይ እና ከበሽታ መጠበቅና መከላከልን፣ የዘር መረጣን፣ የድንች ማጎንቆያ ቤት አሰራር

ወደ ገጽ 5 ዞሯል

# አበይት ዜናዎች

## የምስራቅ አፍሪካን ዘላቂ የውሃ አጠቃቀም እና አስተዳድር ማሻሻል የሚያስችል አውደ ጥናት ተካሄደ

በአምሳሉ ጥላሁን

በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት በኤክስይድ (Exceeded) ፕሮጀክት አዘጋጅነት የምስራቅ አፍሪካ ዘላቂ የውሃ አስተዳድር ማሻሻያ የሚያስችል አመታዊ አውደ ጥናት በባሕር ዳር ከተማ ተካሄደ፡፡

በመርኃ ግብሩ ላይ ተገኝተው የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር ያደረጉት የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩት መምህርና ተመራማሪ እንዲሁም የኤክስይድ ፕሮጀክት አስተባባሪ ዶ/ር ሰይፉ አድማሱ ፕሮጀክቱ በጀርመን ህዝቦችና በአፍሪካ ዩኒቨርሲቲዎች ድጋፍ እንደሚደረግለት ገልፀው በየዓመቱ የሚካሄደው አውደ ጥናት በምስራቅ አፍሪካ የሚታየውን የመሬትና የውሃ አጠቃቀም ችግር ለመፍታት ያለመ እንደሆነ እና በአውደ ጥናቱ ላይ የተሻለ ምርምር ለሚያቀርቡ ምሁራን እንዲሁም ተማሪዎች ዕውቅና ለመስጠት ታስቦ የተዘጋጀ እንደሆነ ዶ/ር ሰይፉ ገልፀዋል፡፡

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ የቴክኖሎጂ ኢንስቲትዩትና የመምህራን ኮሌጅ (ፔዳጎጂ) በ1992 ዓ.ም ይፋዊ ጥምረት በማካሄድ እንደመሰረተና በአሁኑ ወቅት በሀገሪቱ ላይ ካሉ አንጋፋ ዩኒቨርሲቲዎች ውስጥ አንዱ እንደሆነ የገለፁት የኢንስቲትዩቱ የምርምርና የድህረ ምረቃ ት/ቤት ዲን ዶ/ር

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

## ተቋሙ ለተመራማሪዎች የአቅም ግንባታ ስልጠና ሰጠ

በባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ የፔዳጎጂና ትምህርት ምርምር ተቋም ከ2009 ዓ.ም. ጀምሮ የሚሰሩ የምርምር ስራዎች ከተግባር ጋር የተቀናጁ እንዲሆኑ በሚያስችል መንገድ እንዲከናወኑ ለማድረግ ለተቋሙ የምርምር ትልመ ጥናታቸውን አስገብተው ለተመረጡ ተመራማሪዎች የአንድ ቀን ስልጠና ሰጠ፡፡

የተቋሙ ዳይሬክተር ዶ/ር ዳዊት አስራት ስልጠናውን ሲከፍቱ እንደተናገሩት ተቋሙ በያዝነው 2009 ዓ.ም. የሚሰሩ የምርምር ስራዎች የትምህርት ቤት ማሻሻያ ፕሮግራምን (School Improvement Program) መሠረት በማድረግና በዲዛይን ሪሰርች ማለትም ትምህርት ቤቶች በትምህርት ቤት ማሻሻያ ፕሮግራም ረገድ ያሉ ተግባራት ያሉበትን ሁኔታ በማጥናት፣ ከጥናቱ በመነሳት ተግባራቱን ውጤታማ ለማድረግ የሚረዱ ተግባራዊ ርምጃዎችን

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

## ዩኒቨርሲቲው የብሄር ብሔረሰቦችና ሕዝቦችን በዓል አከበረ

በሙሉጐጃም አንዱአለም

በአገር አቀፍ ደረጃ ለ11ኛ ጊዜ የተከበረውን የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ሕዝቦች ቀን «ሕገ መንግስታችን ለዲሞክራሲያዊ አንድነታችንና ለህዳሴያችን» በሚል መሪ ቃል በፓናል ውይይት በባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ተከበረ፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ ለታዳሚዎች የእንኳን አደረሳችሁና የእንኳን ደህና መጣችሁ መልዕክታቸውን አስተላልፈው በዓሉ መከበሩ በህገ መንግስቱ የተደነገገውን የብሄር ብሔረሰቦች መብት እና ዲሞክራሲያዊ ዋስትና እንዲሁም የብሄር እኩልነትን ለመገንባት ጉልህ አስተዋፅኦ እንደሚያበረክት ገልፀዋል፡፡

አንድ ሀገር ያለው ሀብት ለሁሉም ብሄር ብሄረሰብ የጋራ እንደመሆኑ መጠን ይህን የጋራ በዓል ማክበሩ ለሁሉም ማህበረሰብ በራስ የመተማመን አቅሙ ከፍ እንዲልና መብትና ግዴታውን አውቆ አንድ ወጥ የሆነ የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመፍጠር ቁርጠኝነቱን የሚያሳይበት መሆኑን ዶ/ር ባይሌ ተናግረዋል፡፡

በመርኃ ግብሩ ላይ የውይይት መነሻ ሀሳብ ቀርቦ ውይይት የተደረገበት ሲሆን የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች የብሄር ብሄረሰቦችን አልባሳት በመልበስ በዓሉን አድምቀውታል፡፡ የዘጠኙንም ብሄር ብሄረሰብ ባህል አንፀባርቀዋል፤ በተጨማሪም ጥናታዊ ፅሁፍ ቀርቧል፡፡

የዩኒቨርሲቲው የበላይ አመራሮችን ጨምሮ መምህራን፣ የአስተዳደር ሠራተኞች፣ ተማሪዎችና ከውጭ የመጡ እንግዶች በበዓሉ ላይ የተገኙ ሲሆኑ ዩኒቨርሲቲው የሁሉም ብሄር ብሄረሰብ ስብጥር በመሆኑ ተማሪዎች ከቀለም ትምህርት ባሻገር ርዕስ በርዕስ በመቻቻል ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኀበራዊና ባህላዊ እሴቶችን ለማዳበር የበዓሉ መከበር ፋይዳው የጐላ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡

## የሴቶችን ተሳትፎ ለማሳደግ እየተሰራ ነው

በትዕግስት ዳዊት

ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ከሴቶች ስትራቴጂካል ልማት ማዕከል ጋር በመተባበር «ሴቶች አካዳሚያዊ አመራር» በሚል ለሶስት ቀናት የውይይት መድረክ አዘጋጀ፡፡

የማዕከሉ መሥራች እና ዳይሬክተር አምባሳደር ዶ/ር ገነት ዘውዴ ማዕከሉ የተመሰረተው እ.ኤ.አ. ሰኔ 19/2016 ሲሆን የሴቶችን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ለመጨመር እና ሴቶችን በማሳደግ ልማትን ለማስፋፋት ታስቦ የተከፈተ ማዕከል ነው ብለዋል፡፡ የማዕከሉ መለያ «empowering & transforming women's live» ሲሆን የኢትዮጵያ ሴቶችን በኢኮኖሚ፣ በማህበራዊ እንዲሁም በፖለቲካዊ መስኮች ያላቸውን ተሳትፎ ከወንዶች እኩል ለማድረግ እንደሚሰራ ተናግረዋል፡፡ የማዕከሉ ተልእኮ በምርምር ተግባር ተኮር እንዲሁም ችግር ፈቺ የሆኑ ተግባራትን እንደሚያከናውን የሴቶችን አቅም ለሥራ ፈጣራ እና ለአመራርነት ለመገንባት፣ ሴቶች ከወንዶች እኩል ናቸው የሚለውን ግንዛቤ በሁሉም አዕምሮ ለማስረፅ እና ሴቶችን የሚያበረታታ የቴክኖሎጂ እንቅስቃሴ ማምጣት እንደሆነ ዶ/ር ገነት ገልጸዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ፕሬዚዳንት ዶ/ር ባይሌ ዳምጤ የሴት አመራሮች ብዙ ውጣ ውረዶችን አልፈው ስኬታማ ሲሆኑ መንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ባልሆነ ተቋማት ውስጥ ፍትሃዊ የሥራ ክፍፍል እንዲኖር እንደሚያስችል ገልጸው ያለ ሴቶች ተሳትፎ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማኀበራዊ ችግሮች ሊፈቱ ስለማይችሉ ፍትሃዊ የሥራ ክፍፍል እና የሴቶች ተሳትፎ ላይ የበለጠ መሥራት አለብን ብለዋል፡፡

ማዕከሉ በቅርቡ መገናኛ ብዙሃንን በመጠቀም የውይይት ዝግጅት እንደሚጀምር ተናግረዋል፡፡ የተለያዩ ሴቶችን የተመለከቱ ጉዳዮች ከሚመለከታቸው ባለድርሻ አካላት እና ምሁራን ጋር ውይይት እንደሚያደርግ እንዲሁም በአመት አራት ጊዜ የሚታተም «የህይወት ወግ» የሚል የሴቶች መፅሔት ለህትመት በዝግጅት ላይ ይገኛል፡፡ ወደፊት ሥርዓተ ፆታን በሁለተኛ ዲግሪ የሚሰጡ ተቋማት የኢትዮጵያ ሴቶች ላይ ያተኮረ እንዲሆን ሥርዓተ ትምህርት መዘጋጀቱን እንዲሁም ለአስር ሰልጣኞች የአሰልጣኝነት ስልጠና መሰጠቱ ተገልጿል፡፡ ከተለያዩ ዩኒቨርሲቲዎች የመጡ የሴት አመራሮች ምሁራን በውይይቱ በመሳተፍ የህይወት ልምዳቸውን ለተሳታፊዎች ያካፈሉ ሲሆን ብዙ ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበው ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡ በቀጣይ ተመሳሳይ የውይይት መድረክ በመቀሌ ዩኒቨርሲቲ ይካሄዳል፡፡

## የአካል ጉዳተኞች ...

ከገጽ 4 የዞረ

ዳይሬክቶሬት ለአካል ጉዳተኞች እየተደረገ ያለውን ልዩ እንክብካቤና ድጋፍ የሚገልፅ ሪፖርት የቀረበ ሲሆን ዩኒቨርሲቲው ለአካል ጉዳተኛ ተማሪዎች ልዩ ትኩረት በመስጠት በየጊዜው የልዩ ፍላጐት ጥያቄአቸውን አጥጋቢ መልስ በመስጠት ሰፊ ሥራ እያከናወነ መሆኑ ተጠቁሟል፡ ፡ በዝግጅቱ ላይ ጥናታዊ ፅሁፍ ቀርቦ ውይይት ተካሄዷል፡፡ አይነስውራን ተማሪዎች ዝግጅቱን ከመምራት አልፈው የግጥምና የሩጫ ውድድር ብሎም አዝናኝ ሙዚቃዎችን አቅርበዋል፡፡

## የማህበረሰብ አገልግሎት ፕሮጀክት ...

ከገጽ 4 የዞረ

እንዲሁም የምግብ ድንች የማቆያ ቤት አሰራርን ያካተተ ስልጠና ተሰጥቷል፡፡

ፕሮጀክቱን የማስፋፋት ሥራ በ2008 በጀት ዓመት ከ650 ሺ ብር በላይ በመመደብ በአምስት የገጠር ቀበሌዎች በሚገኙ አርሶ አደሮች የሠርቶ ማሳያ ሥራዎች ተከናውኗል፡፡ በ2009 ዓ.ም ሠርቶ ማሳያው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል በጉብኝቱ ወቅት ተገልጿል፡ ፡ በዩኒቨርሲቲው የሰርቶ ማሳያ ድጋፍ 265 አርሶ አደሮችን አሰልጥኖ በማሰማራት በ29.24 ሄክታር መሬት በበለጠ ድንች እና በሮዳስ ሳር እንዲሸፍን ተደርጓል፡፡ ከነዚህ ውስጥም 260 ወንዶች ሲሆኑ 5 ሴቶች ናቸው፡፡ አርሶ አደሮቹ ቴክኖሎጂውን በቅርበት ማግኘት የቻሉ በመሆኑ የቴክኖሎጂውን ሽግግርም የበለጠ እንደሚያፋጥን ተገልጿል፡፡ ወደፊት በወረዳው ያለውን የከብት መኖ እጥረት ለመቅረፍ እንዲሁም የወተት ምርትን ለመጨመር የሚያስችል መሰረት ለመጣል ተችሏል፡፡

## ጽ/ቤቱ ለአመራሮች እና መምህራን ስልጠና ሰጠ

በትዕግስት ዳዊት

የባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚደንት ጽ/ቤት ለአመራሮች እና መምህራን በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት ላይ ያተኮረ ስልጠና ሰጠ፡፡

የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት አዋጅ ከምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት አኳያ፣ የመምህራን መብት እና ግዴታ፣ የውል አያያዝ እና ስምምነትን በተመለከተ የጋራ ተጠቃሚነትን መሰረት ያደረገ መሆን እንዳለበት በአቶ አየነ መንገሻ ቀረበው ህጉን ከተግባር ጋር በማገናኘት እንዴት መሰራት እንዳለበት በተሳታፊዎች ሰፊ ውይይት ተደርጎባቸዋል፡፡

የግዥ ዓላማ እና መርሆዎች፣ የግዥ ሂደት፣ የግዥ ሥራ ክፍል ተግባርና ኃላፊነት በአቶ ምስጋናው ሙጩ እንዲሁም የፋይናንስ ህግና መመሪያው በሥራ ላይ ከገጠማቸው ገጠመኝ ጋር በማገናኘት እንዲሁም የምርምር በጀት ለታለመለት ዓላማ እንዴት መዋል እንዳለበት ያቀረቡት ደግሞ አቶ አዲስ አድማስ ናቸው፡፡

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ለበላይ አካላት

በደስታ ተከስተ
ባሕር ዳር ዩኒቨርሲቲ ፀጥታ አገልግሎት

የመስሪያ ቤቱ አንዳንድ ሰራተኞች በሰሞነኛ ወሬ ተጠምደዋል፡፡ ስለ መስሪያ ቤቱ ብሉሹ የአሰራር ስርዓት ሀሜትና አሉባታ ደርቷል፡፡ አብዛኛው ሰራተኛ እዚህ ተቋም ውስጥ ለመቀጠር ብዙ ጓጉተው ውጣ ውረዶችን አልፈዋል፡፡ ጥቂቶችም በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ስፍራ ለማግኘት ለየ አማልክቶቻቸው እንደተሳሉና ስለታቸው ደርሶ ከወዳጅ ዘመዶቻቸው ጋር በደስታ ጮቤ እንደረገጡ ይታወቃል፡፡ ዛሬ ላይ ግን መስሪያ ቤቱን ለማጥላላትና ለማማረር መብቃታቸው ሁኔታውን ለሚታዘብ ሰው ነገረ ስራቸው ያሸማቅቃል፡፡ እርግጥ ነው አንዳንድ መልካምና በጎ አመለካከት ያላቸው ሠራተኞ ስለ ተቋሙ ጥሩነትና አንዳንድ ችግሮች ቢኖሩም በሂደት ሰራተኛው እራሱ እየታገለ መስተካከል የሚችሉ መሆናቸውን ያስረዳሉ፤ የመስሪያ ቤቱንም ተልዕኮና ራዕይ ዕውን እንዲሆን የበኩላቸውን ይጥራሉ፡፡

‹‹ምን ይሽ መስሪያ ቤት ከውጭ ሲያዩት ስም ብቻ እንጂ ውስጡ ሲፈተሽ የሞተ ነው›› ሲል አንዱ ‹‹ልክ ብለሃል›› እያለ ሌላው ይቀጥላልና ‹‹ይሽ መስሪያ ቤት እኮ መስሪያ ቤት ከሚባል የቤተ ዘመድ ቤት ቢባል ይቀላል፡፡›› ትላለች ሌላዋ የአሉባልታውን መዘውር እያፈጠነች፡፡ ‹‹ኸረ ልክ ብለሻል እቴ! ቅጥርና የደረጃ እድገት ሲወጣ ሁሉ ነገር በዘመድና በእውቂያ ነው፤ እኛ ዘመድ የሌለን ሰው ይኸው ባለንበት ቁጭ በለናል›› አለች በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ብዙ አመታት አንዳሳለፈች ለመግለጥ እየሞከረች፡፡ ‹‹ምን እናንተ ደግሞ የዚህ መስሪያ ቤት ሃላፊዎች እኮ እንዳሉ በሙስና የተዘፈቁ ናቸው ይባላል... ይገርማችኋል! በዚህ ተቋም ውስጥ ኀላፊ ሆኖ›› ሲል አንደኛው ሌላኛው ከአፉ ተቀብሎ « አዎ... ኃላፊ ሆኖ ሁለትና ሶስት መኖሪያ ቤት ያልሰራ፣ በልጆቹና በሚስቱ ስም አክሲዮን ያልገባ? መኪና ያልገዛና በባንክ ገንዘብ ያላስቀመጠ አይገኝም ይባላል!» እያለ የአሉቧልታ ድሩን ሲያከር ሰንብቷል፡፡

በመስሪያ ቤቱ ውስጥ የሚወራው አሉቧልታና ሀሜት አድጐ ስጋ ለብሶ ሊገለጥ ምንም አልቀረውም፡፡ ሠራተኛው ሥራ ከመሥራት ይልቅ ባገኘው አጋጣሚ እየተቧደነ ማውራት ብቻ በመሆኑ ይህን ችግር ለመፍታትና የሰራተኛውን ቅሬታዎች አዳምጦ መፍትሄዎችን ለማስቀመጥ የበላይ አካላት የሚባሉ ሰዎች ወደ ተቋሙ መምጣታቸው በመገለፁ አንዳንድ ሠራተኞች የተደሰቱ ቢሆንም ጥቂቶች ግን «አይይ መስሏቸው ነው እንጂ የዚህን መስሪያ ቤት ችግር እንኳን የበላይ አካላት ቀርቶ ቅዱስ ሚካኤል በዕለተ ቀኑ ከሰማይ ወርዶ ቢመጣ የሚፈታው አይመስልም!» በማለት ሲሳለቁ ተሰምተዋል፡፡

ለመስሪያ ቤቱ ሠራተኞች በሙሉ ለበላይ አካላት የሚያቀርቧቸውን የግል ቅሬታዎችንና ጥቆማዎችን በአካል በመገኘት አልያም በፅሁፍ በፖስታ አሽገው ማቅረብ እንደሚቻል በማስታወቂያ መልክ በተገለፀው መሰረት የበላይ አካላት የተባሉት ሰዎች ለዚሁ አገልግሎት ታስቦ በተዘጋጀላቸው ጊዜያዊ ቢሮ ውስጥ ተሰይመዋል፡፡ በፖስታ ታሽገው የቀረቡ በርካታ ጉዳዮች በፊታቸው ተቆልለዋል፡፡ ከዚህ ሌላ አለኝ የሚሉት የግል ቅሬታና ጥቆማዎችን ለማቅረብ በቢሮአቸው አቅራቢያ የተሰለፉ ሠራተኞች ሲታዩ የሰልፉን ትርምስና ጫጫታ ላስተዋለ ሰው እግዚኦ ያሰኛል፡፡

የቅርብ ኃላፊዎች የተባሉ ግራ ተጋብተው ከቢሮአቸው ወጣ ገባ ይላሉ፡፡ «ለመሆኑ ይህ ሁሉ ሠራተኛ ምን ችግር ቢደርስበት ነው እንደዚህ ነቅሎ የተሰለፈው?» ይባባላሉ እርስ በእርሳቸው፡፡

«እንግዲህ ያው የመጡት የበላይ አካላት ስለሆኑ እንኳን ደህና መጣችሁ ሊሏቸው ይሆናል፡፡» አለ በመቀለድ የሚታወቀው አንደኛው የሥራ ኃላፊ፡፡ «እኔ እስከማውቀው ድረስ ተቋማችን የመንግስትን መመሪያና የአሰራር ስርዓት ተከትሎ ነው እየሰራን ያለነው፡፡ ይህንንም ጉዳይ እራሳቸው የበላይ አካላት ያውቁታል፡፡ የተለየ ነገር በዚህ መስሪያ ቤት ምን እየሆነ እንዳለ አልገባኝም፡፡ አንዳንድ ችግሮች ቢኖሩም ይህን ያህል ሰራተኛ ቅሬታ ይኖረዋል ብዬ አልገመትም ነበር!›› አሉ የመስሪያ ቤቱ ዋና የሥራ ኃላፊ፡፡ ‹‹ጌታዬ አይጨነቁ ሀበሻ ሰልፍና ሀሜት ይወዳል? ይኸኔ አንዳንዱምኮ ሰው ሲሰለፍ አይቶ የተሰለፈ ይኖራል›› አለ ቀልደኛው፡፡ ‹‹አንተ ደግሞ ቀልድና ቁምነገር ትቀላቅላለህ›› አሉት ዋና ኃላፊው ኮስተር በማለት፡፡ ወዲያው በኃሳባቸው እራሳቸው አሉኝ ያሉትን ቅሬታ በወረቀት ላይ ፅፈው በፖስታ አሽገው መስጠታቸው ትዝ አላቸውና ‹‹ስማ እስቲ አንተስ ቅሬታ የለህም እንዴ? ለምን ሄደህ አልተሰለፍክም?›› አሉት ጓደኛቸውን፡፡ ‹‹እኔ ሰልፍ አልወድም፤ ሰው ተሰልፎ ሳይ ያኔ በደርግ ዘመን ልጅ እያለሁ ቀበሌ ዳቦ ለመግዛት በሰልፍ ማህል ገብቼ የሆንኩትን ገጠመኝ ያስታውሰኛል፤ ቅሬታ ቢኖረኝም ያው እንደሰለጠነ ሰው ያለኝን ጉዳይ በፁሁፍ አስገብቻለሁ›› ሲላቸው ‹‹ጥሩ ነው›› አሉ ዋና ኃላፊው፡፡



...

‹‹እሺ እሜቴ የእርስዎ ጉዳይ ምንድን ነው?›› አሉ ከቅሬታ ሰሚዎች አንደኛው ሰውዬ በተሰላቸ ሁኔታ፡፡ እስካሁን ያደመጧቸው ሰራተኞች ጥያቄዎቻቸውና ቅሬታዎቻቸው ተመሳሳይ በመሆኑ አንዱ መጥቶ ሌላዋ ስትገባ የተለዩ ጉዳይ ይመጣ ይሆናል ብለው በትዕግስት ይጠብቃሉ፡፡ ‹‹እ... እ... እኔ እንግዲህ ዋናው ቅሬታዬ እዚህ መስሪያ ቤት ሥራ ከጀመርኩ ጀምሮ በብዙ ችግር እየተሰቃየሁ ነው፡፡ በስራዬ ላይ ብዙ አመታት ባስቆጥርም እድሜ እንጂ የደሞዝ እድገት አልገጠመኝም›› ከማለታቸው ‹‹በምን የሥራ መደብ ላይ ነው እየሰሩ ያሉት?›› አለ ቅሬታ ተቀባዩ በማስታወሻ ደብተሩ ላይ እየፃፈ፡፡ ቀጠሉ ሴትዮዋ ‹‹አዎ መደብ ማለታችሁ ልክ ናችሁ! ድሮስ ድሃ መደብ ላይ እንጂ ሞዝቮልድ አልጋውንማ የታባቱ ያገኘውና ነው›› እንዳሉ ሶስቱም ፈገግ አሉ፡፡ ‹‹በምን ሥራ ላይ ነው እየሰሩ ያሉት ማለታችን ነው እሜቴ» አለ አንደኛው ሰው ፡፡ ‹‹ፅዳተኛ ነው፡፡ ይኸውና በፅዳት እየሠራሁ ብዙ አመት ሆኖኛል መቼም የፅዳተኛ ደሞዝ ምን ያህል እንደሆነ እናንተም የበላይ አካላት ታውቁታላችሁ›› ብለው ዝም ሲሉ ‹‹ያው እኛ እንደተረዳነዎት የእርስዎ ቅሬታ ደሞወዝ አንሶናልና ይጨመርልኝ ማለት አይደለም?›› ሲሏቸው ‹‹አይ ሄ... ሄ የምን ይጨመርልን ብቻ እየተከፈለን ስላልሆነ ይከፈለን ነው እንጂ! ስሙ እንጂ ደሞዝ የሚባለው... ›› አሉና ከንፈራቸውን በሀዘኔታ ለራሳቸው መጠጡ፡፡

‹‹ለመሆኑ ምን ያህል ቢከፈልዎት ይመኛሉ?» ሲባሉ እንደ ማስላሰል አሉና ‹‹መቸም መንግስት እጁ ሰፊ ነው፤ ምን አለበት ሁለት ሺ ብር አድርጎልን ይኸን ፅዳተኛ ሁሉ አፉን ቢያዘጋው›› ሲሉ ‹‹ሁለት ሺ ብር ቢከፈል ይበቃል ብለው ያስባሉ?›› ሲሏቸው ‹‹ኸረ እዲያ! እነደው ዝም ብዬ እንጂ የኑሮ ውድነቱን ታውቁታላችሁ! መቸስ ለእንደኔ አይነቱ እንደነገሩ ቢሆንም ከምንም ይሻላል፤ እኔማ መድሃኒአለም ምስጋና ይግባውና በደህናው ዘመን የሰራሁት ቤት አለኝ፣ ከኪራይ ከማገኘው ጋር ተጨምሮ ውዬ እንዳድር ያደርገኛል›› ሲሉ ‹‹ብዙ ቤተሰብ አለዎት?››ሲሏቸው ‹‹አዎ ልጆች አሉኝ፡፡ ምስጋና ለፈጣሪ ሁለታቸውም እራሳቸውን ችለውለኛል፡፡ እኔንም እየረዱኝ ነው፤ እኔም እቤት ተቀምጬ ከምውል ብዬ ነው እንጂ እነርሱማ ስራው ምን ያደርግልሻል? ይቅርብሽ! እኛ ለአንቺ አናንስም እያሉኝ ነበር፡፡ እኔ ደግሞ ለምን ብዬ ለማን ደስ ይበለውና ነው ጡረታዬን ሳላስከብር ስራውን የምተወው በማለት ይኸውና ደከመኝ ሰለቸኝ ሳልል እየሠራሁ ነኝ፡፡ ይገርማችኋል አሁን የሚቀጠሩ ወጣቶች በአንቺ ደሞዝ ወጣት ሥራ አጥ ይቀጠርበት ነበር ለምን ለቀሽ አትወጭም? እያሉ ያሸሟጥጡኛል፡፡ መቼም በሥራ ከእነርሱ አንሼ አላውቅም ኮ! ›› እያሉ ሲናገሩ ‹‹ይበቃል እሜቴ ቅሬታዎትን ተቀብለናል መልስ እስከንሰጥበት ከሌላው ሠራተኛ ጋር ውጭ ይጠብቁ›› ብለው አሰናበቷቸው፡፡

ተረኛ ቅሬታ አቅራቢው እንደገባ በተጠንቀቅ ቆሞ በወታደራዊ ሁኔታ ሰላምታ ሲሰጥ ‹‹እናመሰግናለን ተቀመጥ›› ተብሎ እንደተቀመጠ ‹‹እሺ አለኝ የምተለውን የግል ቅሬታህንና የመስሪያ ቤቱን ችግሮች መጠቆም ትችላለህ›› ሲባል ‹‹በእ... ውነቱ እናንተ የበላይ አካላት መጥታችሁ የሠራተኛውን ብሶት አድምጣችሁ ምላሽ ለመስጠት በመዘጋጀታችሁ በጣሙን ደስ ብሎኛል፡፡ እኔ በዚህ መስሪያ ቤት በጥበቃ ሥራ ላይ እያገለገልኩ እገኛለሁ፡፡ የሥራ ልምዴ ቢጠና ሀገሬን በወታደርነት ለበርካታ አመታት ያገለገልኩበት መስረጃ አለኝ፤ ከወታደርነት በቦርድ ከተሰናበትኩ ጀምሮ እዚህ መስሪያ ቤት ተቀጥሬ መስራት ከጀመርኩኝ አንስቶ የምሰራው ስራና የሚከፈለኝ ደሞዝ ስለማይመጣጠን መንግስት ጉዳዩን አይቶ የደሞወዝ›› ከማለቱ ‹‹እሺ ገብቶናል የአንተም ጥያቄ ደሞዝ ይጨመርልን ነው አይደለም?›› አሉት ከቅሬታ ተቀባዮቹ አንደኛው፡፡ ‹‹ትክክል ነው›› አለ ሰውዬው አንገቱን እየነቀነቀ» ‹‹ሌላስ ስለመስሪያ ቤቱ አሰራር ስርዓት የምታውቀው ችግር ካለ ጥቆማ መስጠት ትችላለህ›› ሲባል ‹‹እኔ መቼስ እከማውቀው ድረስ ስራዬን በሚገባ በታማኝነት እየሠራሁ እገኛለሁ፡፡ ስለ መስሪያ ቤቱ የአሰራር ስርዓት ጥሩ ነው፤ የማውቀው የተለየ ጉዳይ አልገጠመኝም›› ‹‹እሺ ቅሬታህን ተቀብለናል›› በማለት ሲያሰናብቱት እንደአገባቡ ወታደራዊ ሰላምታ ሰጥቶ ወጣ፡፡

‹‹የአንተ ቅሬታ ምንድን ነው›› አሉ ማህል ላይ የተቀመጡ ቅሬታ ሰሚው ‹‹እኔ በዚህ መስሪያ ቤት በሹፌርነት ሙያ ተቀጥሬ የማገለግል ሠራተኛ ነኝ፤ እንደሚታወቀው የሹፌርነት ሙያ ጥንቃቄ፣ ማስተዋልና ትዕግስትን የሚጠይቅ ሥራ ነው፡፡ ስለሆነም እኔም በዚሁ ሁኔታ ስራዬን በተገቢው እየሠራሁ ሲሆን መስሪያ ቤቱ በተለያዩ አካባቢዎች እየተዘዋወረ የሚሠራው ሥራ ብዙ ከመሆኑ አንፃር ከወር እስከ ወር ሥራዬ መስክ በመውጣት ስለሆነ የምሰራው ሥራና የሚከፈለኝ የቀን ውሎ አቦል እንዲሁም ወርሃዊ ደሞዜ አነስተኛ በመሆኑ መስሪያ ቤቱ የውሎ አበልና ደሞዝ ጭማሬ እንዲያደርግልኝ በማለት ቅሬታዬን አቀርባለሁ!›› እንዳለ ‹‹ጥሩ በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ያለው የስምሪት አገልግሎትና በአንዳንድ ሹፌሮች ላይ የሚታዩ የስነ-ምግባር ግድፈቶችን ሰምተናል፡፡ ለአብነት አንዳንድ ሹፌሮች ነዳጅ ይሸጣሉ፤ አዲስ ጎማ በአሮጌ ጎማ ቀይረው ይሸጣሉ፣ መስክ ሲላኩ በመንግስት መኪና ንግድ ያካሂዳሉ፣ ... የሚሉ ጥቆማዎች ይሰማሉና አንተ ምን ትላለህ?›› ሲሉት ቁጣ በፊቱ ላይ እየተገለጠ ‹‹ማነው እንዲህ እያለ የሚያወራው? ውሸት ነው፡፡ እናንተ ስለማታውቁት ነው እንጂ የዚህ መስሪያ ቤት ሰራተኛ አብዛኛው አሉባልተኛና ወሬኛ ነው፤ በተለይ በእኛ በሹፌሮች ላይ አይኑ ደም ይለብሳል፡፡ መስክ ሄደን ስንመጣ ብር ጭነን የምንመለስ ይመስለዋል፡፡ ወደ ሌላ ቦታዎች ስንላክ ከሰል አምጡልኝ፣ እዚህ ቦታ ላይ እንዲህ ያለ እቃ እርካሽ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ከጎዳናው በፊት

በቤተልሄም ሃይለማርያም
፫ኛ አመት የኢኮኖሚክስ ተማሪ
www.Facebook.com/Bethelhem Hailemariam

ሞትን ይረታ ዘንድ የሚቻለው ከወዴት አለ? ጭካኔውንስ ድል ሊነሳ የሚችል ጋሻና ጦር ከየት ይመዘዛል? ንጉስ በግዛቱ ስፋትና በወታደሩ ብዛት ቆነጃጅት በደም ግባታቸውና በቁመናቸው መነኮሳት በምህላቸውና በፀሎታቸው ሊያርቁት የማይቻላቸው ሃያሉን መላክተኛ ሞትን ሊረታው የተገባው አቅም ከምን ይገኛል? በወርቅና በእንቁ የማይሸነግሉት መጎሳቆልና መጎዳት የማያሳዝኑት እንደሞት ያለ ልበ ደንዳና በየትኛው ዘመን ሊፈጠር ይችላል?

ወደ ቀብር ስነስርአት ከሚሄዱት ሰዎች መካከል አንድ የደከሙ ሽማግሌ እንባ ሊያጥበው የማይችል ሀዘን ውስጣቸውን እያላመጣቸው የኑሮ መዳፍ በሻከረው ድምፃቸው ብሶታቸውን ያንጎራጉራሉ፡፡ "ህ. . .ህ ልጄ መጠጊያዬ፣ የእርጅና ድጋፌ፣ የምሽት መጠለያዬ፣ ከዘራዬ ልጄ፣ መቋሚያ ልጄ ህ. . .ህ" ቃላት የሚያወጣውን የውስጣቸውን ነበልባል የሚያበርዱበት ሲያጡ በሚንቀጠቀጡ ጣቶቻቸው የጨበጡትን ከዘራ ጠበቅ እንዳደረጉ ወደ ላይ ቀና ብለው መሃረብ በያዙበት እጃቸው ሰማዩን እየጠቆሙ "እውነት በዙፋንህ አለህ?. . . ህህ እውነት ይህ ነው ጌትነትህ? ይህ ነው ፍርድህ? ህህ" ይጨርሱት ዘንድ አልተቻላቸውም፡፡ ስብራታቸውን የሚገልፅ እንጥፍጣፊ ጉልበት በውስጣቸው አልቀረም፡፡ ከንፈራቸውን ነክሰው "እህህ. . ." እያሉ ለቀስተኛውን ይከተላሉ፡፡

ከወዲያ ከላይ ከደረበው ጥቁር ጨርቅ ይልቅ ጥቁርነት ልቡን የከበበው ጎልማሳ እንባውን እንደ ሃምሌ ዝናብ እየዶፈ በሚንቀጠቀጥ የወንድ እንጉርጉሮ ብሶቱን ያላዝናል፡፡ ". . .ገበና ጓዳዬ! አይዞህ ባይ ደጋፊ ረዳቴ ምርኩዜ! ሚስቴ ልበልሽ እናቴ. . .ህ.. .ህ. . .ህ ወዴት ልሂድ? ጨለመብኝ ጊዜ ፊቱን አዞረብኝ. . .ህ. . .ህ. . . ለማን ልንገር ለማን ላውራ ዙሪያ ገባው ሆነ ኦና . . . ሚስቴ ልበልሽ እናቴ እናቴ ልበልሽ ሚስቴ. . . ደጁ ተዘጋ የቤታችን ምሰሶው ፈረሰ. . . የቤታችን መኝታችን ሳቅ ናፈቀው. . . አንሶላችን ደም አነባ. . . ልጆቻችን በረዳቸው አጉራሽ አጥተው እራባቸው. . . እኔ አላውቀም ምን ይዋጠኝ ምን ላርገው? . . .ህህህ. . . የት ሄደች ልበላቸው ለእነ ሚጣ ምን ብዬ ልንገራቸው፣ ህህ. . . ተሰበርኩ. . .በረደኝ አይዞህ ባይ አጣሁ አለሜ፡፡

ናፈቅሽኝ. . . የክፉ ቀኔ. . . ሚስቴ ምነው ሲነጋ ሄድሽ? ምነው ያቀን ሲያልፍ ራቅሽ? . . . ሚስቴ ልበልሽ እናቴ፣ እናቴ ልበልሽ ሚስቴ. . ..እህ እህ" ቃል አያልቅበትም፡፡ ጥሪ ይመልሳት ይመስል የሬሳ ሳጥኑን እየተከተለ እየተንሰቀሰቀ፣ እየተርገፈገፈ፣ እየጮኸ ይጣራል ያለቅሳል፡፡ በወንድ አንጀቱ እንስፍስፍ እያለ. . . መደማመጥ የለም እንባ እንደኖህ ዘመን ዝናብ ይፈሳል፡፡ በሞት ጆሮ ግንድ ላይ የሃዘን ድምር ያጓራል፡፡

ደሞ ከወዲያ ጥግ ሁለት ተመሳሳይ ልብስ የለበሱ ሁለት ህፃናት ሰው ሁሉ እነሱን እያየ ከንፈር ሲመጥ በፍርሃት እየተያዩ እንባቸውን በሹራባቸው ጫፍ እየሞዠዠቁ ለምን እንደሚሄዱ ሳያውቁ ኩስ ኩስ እያሉ ህዝቡን ይከተላሉ፡፡

ይጮሃል፣ ይለቀሳል. . . እዬዬ. . . እሪታ. . . እንባ. . . ጩኸት ተቀላቅለው በመለየትና በሸኝት ጎዳና ይጓዛሉ፡፡

ከዚህ በኩል ደግሞ ሶስት ሰዎች የደገፏት ሴት እግሮቿ የራሷ እስከማይመስሉ ድረስ ማንሳት እየከበዳት በደረቀ ጉሮሮ በተሳሰረ ምላስ "ጓዴ. . . እህቴ መደበቂያ. . .ጥጌ. . . መካሪ ተቆጪዬ ከፋኝ እህት አለም አፅናኝ አጣሁ፡፡ ጓዴ መሶቤ ጎደለ. . . ባለእንጀራዬ ማናላት ብለሽ ሳትነግሪኝ ሄድሺ? ተደባብቀን አናውቅም እኮ. . . ህ. . .ህ" ሆሄያት ከላንቃዋ እየተሰነቀሩ አልተፋ ሲሏት ሳል ይከተላታል፡፡ እዬዬ. . .እሪታ. . .ጩኸት መደማመጥ የለም፡፡ ከፊት አልቃሾች ልብ በሚሰብር ዜማ ደረታቸውን ይደቃሉ፡፡ ወንዶች ጋቢያቸውን ተሸፍነው እያልጎመጎሙ ያዜማሉ፡፡

ሙሉሉሉታ እስከዚያኛው ሰማይ!

ደሞ ሌላ ከዚያኛው ጥግ፤ የታዘለች ህፃን ቋንቋ የሌላት፣ ታስረዳበት ዘንድ አንደበቷ ያልጠነከረ አንቀልባ የደገፋት ህፃን፡፡ የሽፈናትን ጥቁር ፎጣ በልጦ የሚወጣ ጩኸት-እሪታዋን ታስነካዋለች፡፡ ይሄኛው እዬዬ ቃል የሌለው ህመም ነው፡፡ መግጠም፣ ማዜም፣ መጣራት ያለየለት ያመረረ እንባ ነው፡፡ ወራት ያላለፉት ህፃን ከታዘለችበት አንቀልባ ዘልቆ የተሰማት የመለየት አለንጋ ያለቋንቋ ያስነባታል፡፡ እማዬ. . . እማዬ ትል ዘንድ ቃል የሌላት መሰበሯን በእሪታዋ ታዜማለች፡፡

. . .ሌላም. . . ሌላም እልፍ.. .ህመምና ለቅሶ

ድብልቅልቅ ጥሪ ተመሳሳይ ሃዘን፣ የማይደመጥ ዜማ አንድ አይነት ስብራት፣ መለየት፣ መነጠቅ ማጣት፣ እገሌ ለነበረው ሰው ሬሳ ይሉት ስየሜ ሰጥቶ በጣውላ በተሰራ አጥር አሽጎ ወደ ስሪቱ መመለስ፡፡ እያንዳንዱ ሰው አንድ አካል መቀማት ከሽማግሌው ልጅ፣ ከጎልማሳው ሚስት፣ ከዛች እሪታዋ ከማይደመጥ እናት መንጠቅ ሞት ብቻ ሊበይነው የሚችል ፍርድ ነው፡፡ ይከሰስ ዘንድ ሽንጎ ይበቀሉት ዘንድ ሃገር የሌለው ሽፍታ፡፡ ካንኳኳ የማይመለስ፣ ባለቤት የማያስፈቅድ እንግዳ፡፡ የእንባ ጎርፍ የማይገፋው ሸክም፡፡

ሁሌም እንደዚህ አለ፡፡ ሁሌም እንደዚህ ሸኝት አለ፡፡ ዛሬ አድርሶ የመጣ ነገ ጎዳናው የእርሱ ነው፡፡ ትናንት ማጣት እንዲህ ነበር፤ ዛሬም እየሆነ ነው፤ ነገም አይቋረጥም፡፡

ይህ ጥሪ ማንንም አያልፍም፣ ማንም ሊደበቀው አይችልም፡፡ እንደ አጋፋሪ እንዳሻው በበቅሎ መገኛውን ቢለዋውጥም. . .

መውጣትና መውረድ፣ መሰበር መቃናት፣ ግፊያና ግርግር. . . ሌላም ሌላም ትርምስ ቀስት ወደ ጥሪው ነው፡፡ ወደዚያ መቅረትን ወደማይቀር ጣሪያ ማፍሰስ፡፡

ዳሩ ይህ ሁሉ ውጥንቅጥ መድረሻው አንድ ቢሆንም ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም፡፡ ይልቁስ ከጥሪው ወቅት በፊት ልንሰበስበው የሚገባን አዝመራ አለ፡፡ ለመጪዎች በጎተራው ሞልተን ልናቆያቸው የሚገባ ፍሬ ከዚህ አለ፡፡ ያ ፍሬ ደግሞ መልካምነት ነው፡፡ በይቅርታ ጥማድ ታርሶ በበጎነት የሚታጨድ፣ በቅንነት ጉልማ ተዘርቶ በጥሩ አሳቢነት አውድማ የሚወቃ ፍሬ፡፡ ያቺ ሴት ያን ሁሉ ፍቅር አትመለስበት ሄዳለች፤ ሁላችንም እንደዛው ነን፡፡ ለዛ ደግሞ እስካለን ድረስ ይቺው ትግላችን በቅንነት ርምጃ ትሞላ፡፡

ይህ ሁሉ ውጥንቅጥ መድረሻው አንድ ቢሆንም ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም፡፡ ይልቁስ ከጥሪው ወቅት በፊት ልንሰበስበው የሚገባን አዝመራ አለ፡፡ ለመጪዎች በጎተራው ሞልተን ልናቆያቸው የሚገባ ፍሬ ከዚህ አለ፡፡

ስጋ ሲከተት ማንም በመጥፎ አያንሳን፤ ያስከፋነው አይኑር፤ ለዛ የመልካምነት ፍሬ ራስ ወዳድነት ቃርሚያው ነው፡፡ እኛ ደግሞ በፍሬ የተገነባን ነንና ቃርሚያውን ለወፎች ትተን በምርቱ ጎተራችን ይሙላ፡፡ ያ የትእዛዝ ጎዳና እንባና እሪታ የማይንደው ከእስትንፋሳችን ጋር የተገመደ ክታብ ነው፡፡ ከዛ በፊት ግን በቅንነት መሰላል ዘመናችን ታላቅ ይሁን፡፡ ከጎዳናው በፊት ግን በጊዜያችን ላይ እንሰልጥንበት፡፡

## የምስራቅ አፍሪካን ዘላቂ የውሃ …

ከገጽ 5 የዞረ

አትክልት አበበ ናቸው፡፡ ዩኒቨርሲቲው በአሁኑ ወቅት በመማር ማስተማር፣ በምርምርና ማህበረሰብ አገልግሎት አመርቂ ሥራዎችን በመሥራት ላይ እንደሚገኝና በአሁኑ ሰዓት ከ52000 በላይ ተማሪዎችን በማስተማር ላይ ያለ ዩኒቨርሲቲ እንደሆነ ገልፀዋል፡፡ የአፍሪካ ዕድገት ውሃን መሰረት ያደረገ እንደሆነ እና አብዛኞዎቹ ሀገራት በግብርና ኢኮኖሚ ላይ የተመሰረተ ልማት በመሆኑ ለእርሻና ለሀይል አቅርቦት ትኩረት ሊሰጠው ስለሚገባ በአውደ ጥናት ላይ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ዶ/ር አትክልት አሳስበዋል፡፡

የውሃ አጠቃቀምና አስተዳድር የአፍሪካ ችግር ብቻ ሳይሆን የምስራቅ ኤዥያ፣ ላቲን አሜሪካና መሰል ታዳጊ ሀገራት ችግር እንደሆነ የገለፁት የምስራቅ አፍሪካ የኤክስይድ ፕሮጀክት አስተባባሪ ዶ/ር ሳሙኤል ፓሪ ናቸው፡፡ ውሃን በአግባቡ ማስተዳደርና መጠቀም እንዲሁም የንፁህ መጠጥ ውሃ ችግር ለመቅረፍ አካባቢያዊ ቁሳቁሶችን ጥቅም ላይ ማዋል እንደሚገባ እና ለአካባቢያዊ ችግር አካባቢን መሰረት ያደረገ መፍትሄ መስጠት እንደሚገባ ተናግረዋል፡፡

በአውደ ጥናቱ ላይ ከጀርመን፣ ከኬንያ፣ ከቡሪኪናፋሶ፣ ከቶጐ፣ ካሜሮን እንዲሁም ከኢትዮጵያ የግሎባል ኔትወርክ አባል የሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች የተሳተፉ ሲሆን የተመረጡ የምርምር ሥራዎችም እውቅና ተሰጥቷቸዋል፡፡ በተለይ የሁለተኛና የሶስተኛ ዲግሪ ተማሪዎች በዚህ አውደ ጥናት ላይ ተሳታፊ መሆናቸው ብዙ ልምድ ያገኙበት እንደነበር ገልፀዋል፡፡

## ማዕከሉ ዓለም አቀፍ …

ከገጽ 4 የዞረ

አምስቱ በዚሁ አውደ ጥናት ላይ ቀርበው እንዲወዳደሩ እንደተደረገና አሸናፊዎችም ሆኑ ተሸናፊዎች ወደ ማዕከሉ በመቅረብ ተገቢውን ድጋፍ እንደሚያገኙ ተናግረዋል፡፡

የዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ፣ ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ ሴክተር መስሪያ ቤቶች የተውጣጡ እንዲሁም በሙያው የካበተ ልምድ ያላቸው ግለሰቦች በአውደ ጥናቱ ላይ የተሳተፉ ሲሆን የኢንተርፕርነርሽፕ ስነ-ምህዳር ምን እንደሚመስል የሚያሳዩ የተለያዩ ጥናታዊ ፅሁፎች ቀርበው ሰፊ ውይይት ተካሂዷል፡፡ በሙያው ስኬታማ የሆኑ ግለሰቦችም ያላቸውን ልምድ ለታዳሚው አካፍለዋል፡፡

ተሳታፊዎችም ከአውደ ጥናቱ ስለ ኢንተርፕርነርሽፕ ብዙ ነገር መቅሰማቸውን ገልፀው ብዙ መሥራት እራስን ከመቻል አልፎ የሌላውንም ትኩረት እንደሚስብ በአንክሮ ተናግረዋል፡፡ የተመረጡት አምስት የሥራ ፈጣራ ዘርፎች በተሳታፊዎችና በሙያው ጥልቅ እውቀት ባላቸው ሰዎች ተገምግመው ሶስቱ ያለፉ ሲሆን ሁለቱ ጅምራቸው ጥሩ ቢሆንም በፅንሰ ሀሳብ ደረጃ ላይ ያሉ በመሆናቸው በቀጣይ በደንብ እንዲሰሩና ውጤታማ መሆን እንዲችሉ ከገምጋሚ ዳኞች ማሳሰቢያ ተሰጥቷል፡፡ ፅንሰ ሀሳቡን ወደ ተግባር እንዲቀየር አስፈላጊዉን ሁሉ ትብብር እንደሚደረግ ለስራ ፈጣራ ተወዳዳሪዎች ተገልጿል፡፡

# እንግዳችን

## “የታካሚዎቼን ደህንነት በመጠበቅና መልካም አርአያ በመሆን የምችለውን ሁሉ በመስራት ለዩኒቨርስቲው መልካም ስም ጉልህ አስተዋፅኦ አበረክታለሁ፡፡”

ዶ/ር አክብረት ሰመረ

**የዚህ ወር እንግዳችን በባሕር ዳር ዩኒቨርስቲ ከህክምናና ጤና ሳይንስ ኮሌጅ በ2009 ዓ.ም ከፍተኛ ውጤት በማስመዝገብ የማዕረግ ተመራቂ የሆነችውና አሁን ዩኒቨርስቲውን ከተማሪነት ወደ መምህርነት የተቀላቀለችው ዶ/ር አክብረት ሰመረ ናት፡፡ ዶ/ር አክብረት የህይወት ተሞክሯዋን ልታጋራን ከናይል ጋዜጣ ዘጋቢ ሙሉጐጃም አንዱአለም ጋር ቆይታ አድርጋለች፤ ቃለ መጠይቁን እነሆ፤ መልካም ንባብ!**

ናይል ፡- በመጀመሪያ ስምሽንና የልጅነት አስተዳደግሽን ብታጫውችን?

ዶ/ር አክብረት ፡- ስሜ ዶ/ር አክብረት ሰመረ እባላለሁ፡፡ የልጅነት አስተዳደጌ ያው እንደ አብዛኛው ኢትዮጵያዊ ልጅ ነው፡፡ የተወለድኩት በመቀሌ ከተማ ሲሆን እድገቴ አዲስ አበባ ሆኖ እድሜዬ ለትምህርት እንደደረሰ የመጀመሪያ እና የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቴን “በብራይት ፊውቸር” ት/ቤት ተከታትዬ ጨርሻለሁ፡፡ ለቤተሰቦቼ የመጀመሪያ ልጅ ነኝ፡፡

ናይል ፡- ያስመዘገብሽው አማካይ ውጤት (CGPA) ስንት ነው?

ዶ/ር አክብረት ፡- አጠቃላይ ውጤት 3.67 ነው

ናይል ፡- የሕክምና ሙያ በልጅነትሽ የምትመኚው ነበር? እንዴት መረጥሽው?

ዶ/ር አክብረት ፡- የሕክምና ትምህርት የተመኘሁት 11ኛ ክፍል ተማሪ እያለሁ ነበር፡፡ ቤተሰቦቼ የሕክምና ባለሙያ ስለሆኑ ከልጅነቴ ጀምሮ የሚሰሩትን ሥራ ሳይ ደስ ይለኝ ነበር፡፡ በተለይ አንድ ታካሚ ድኖ ከሆስፒታል ሲወጣ እናትና አባቴ በደስታ ሲያወሩ ስሰማቸው ይመስጠኝ ነበር፡፡ ይሄ አጋጣሚ የሕክምና ትምህርት እንድመርጥ ተፅዕኖ አድርጐብኛል ብዬ አስባለሁ፡፡

ናይል ፡- የሕክምና ትምህርት ላንቺ እንዴት ነበር?

ዶ/ር አክብረት፡- የሕክምና ትምህርት ለኔ የእውነት የልፋት ዋጋ የሚገኝበት አስደሳችም አድካሚም ነው፡፡ ከሁሉም በላይ ግን ትግስት፣ ርህራሄ እና ፍቅር የምትማሪበት ሙያ ነው፡፡

ናይል፡- ከተመራቂ የሕክምና ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት በማምጣት የወርቅ መዳልያ ተሸላሚ ሆነሻል፡፡ ለዚህ ስኬትሽ ሚስጥሩ ምንድን ነው?

ዶ/ር አክብረት፡- መጀመሪያ የስኬቴ ሁሉ መሰረት የእግዚአብሄር ፍቃድ ነው፡፡ ከዛ በተጨማሪ አንድ ሰው የሚችለውን ሁሉ ለመፈፀም መጣር፣ ትዕግስት እና መልካም አመለካከት ናቸው ለስኬቴ ሚስጥር ብዩ የምወስደው፡፡ ምክንያቱም አንድ ሰው መስራት ለሚፈልገው ሁሉ ቀና /ፖዘቲቭ/ አመለካከት እና ማድረግ እችላለሁ የሚል ወኔ ካለው የትም ቦታ መድረስ እንደሚችል ስለማምን ነው፡፡

ናይል፡- በግቢ ቆይታሽ የተደሰትሽበት እና ያዘንሽበት የማይረሳ አጋጣሚ ካለሽ ብታጫውችን?

ዶ/ር አክብረት፡- ብዙ አጋጣሚዎች አሉ ግን የምርቃቴ ቀን በጣም ከተደሰትኩባቸው ቀናት አንዱና ዋናው ነው፡፡ ያዘንኩበት አጋጣሚ ብዙ አለ፡፡

ናይል፡- በዩኒቨርስቲው ቆይታሽ ከቀለም ትምህርት በተጨማሪ የተማርሽው ነገር ምንድን ነው?

ዶ/ር አክብረት፡- ከተማርኩት ነገር የማህበራዊ አኗኗር አንዱ ነው፡፡ እያንዳንዱ ሰው የተለያየ ባህሪ አለው፡፡ ያንን አቻችሎ መኖር ትልቅ ትዕግስት ይጠይቃል፡፡ በግቢ ቆይታዬ ትልቁ የተማርኩት ትዕግስት እና ራስን ችሎ መኖር ነው፡፡

ናይል፡- የግቢ ማህበራዊ ሕይወት እንዴት ነበር?

ዶ/ር አክብረት፡- የማህበራዊ ሕይወቴ ከሞላ ጐደል መልካም ነበር ለማለት ይችላል፡፡ ነገር ግን ብዙ ፈተናዎች ነበሩ፡፡ በዚህ ውስጥ ግን ፍቅርን፣ ትዕግስትን፣ ተቻችሎ መኖርን፣ ደስታን እና ድካምን አይቼበታለሁ፡፡



ናይል፡- የሕይወት ፍልስፍናሽ (መርሕሽ) ምን ይመስላል?

ዶ/ር አክብረት፡- ማንም ሰው ጠንክሮ ከሰራ ከፈጣሪ ጋር የፈለገበት ቦታ መድረስ ይችላል የሚል አቋም አለኝ፡፡

ናይል፡- እዚህ ደረጃ ለመድረስ አርአያ ወይም ሞዴል አድርገሽ የምትወስጅው ማንን ነው? ለምን?

ዶ/ር አክብረት፡- ለእኔ ሞዴሎቼ እናትና አባቴ ናቸው፡፡ በህይወታቸው በጣም ብዙ ለመናገር የሚከብዱ ፈተናዎችን አልፈው ልጆቻቸውን እዚህ ደረጃ አድርሰዋል፡፡ እኔም የአላማ ፅናትና ትዕግስት መጀመሪያ የተማርኩት ከእነሱ ነው ማለት እችላለሁ፡፡ በሁሉም መንገድ ከጐኔ ሆነው ስለደገፉኝ በዚህ አጋጣሚ እነሱን ማመስገን እፈልጋለሁ፡፡

ናይል፡- የአጠናን ዘዴሽ ምን ይመስላል?

ዶ/ር አክብረት፡- የአጠናን ዘዴዬ ቀላል ነው፡፡ ያው ከክላስ በኋላ ቀን አነባለሁ፤ ከዛ ማታ በጊዜ ጀምሮ በቂ እንቅልፍ እተኛለሁ፡፡ ነገር ግን የጥናት ሰአቴን በምንም ምክንያት አላባክንም፡፡ በየቀኑ የተማርነውን ስለማነብ ለፈተና ብዬ እንደ አዲስ አልጨናነቅም፡፡ በተለይ ግን መፅሀፍቶችን ማንበብ ስለምወድ ብዙ እውቀት አግኝቼበታለሁ፡፡ ነገሮችን ሰፋ ባለ መንገድ ለመረዳት መፅሀፍት በጣም አጋዥ ናቸው፡፡ አብዛኛው የራስ ጥረት ስለሆነ ብዙ መስራት ስለሚጠበቅብኝ የምችለውን ሁሉ በእግዚአብሄር ፍቃድ ለማድረግ እሞክራለሁ፡፡

ናይል፡- ወደፊት ምን መሥራት አስበሻል? የዛሬ አስር አመት ራስሽን የት

⇨

# እንግዳችን ...

አገኘዋለሁ ብለሽ ታስቢያለሽ?

ዶ/ር አክብረት፡- ወደፊት በህክምና ሙያው በመቀጠል የትምህርት ደረጃዬን በማሻሻል ህዝቤን ለማገልገል አስባለሁ። እንደ ፊጣሪ ፍቃድ Cardiology ወይም የልብ ህክምና በማጥናት ብዙ ሰው ለመርዳት አስባለሁ። ከዛም በተጨማሪ መልካም ቤተሰብ መስርቼ መኖር ምኞቴ ነው።

ናይል፡- ከትምህርትሽ ጐን ለጐን ያበረከትሻቸው አስተዋፅኦዎች ካሉ ብትገልጭልን?

ዶ/ር አክብረት፡- ከትምህርት ውጭ ከተሳተፍኳቸው አንዱ የደም ልገሳ ፕሮግራም ላይ ነው። ደም መለገስ በጣም አስደሳች እና የህሊና እረፍት የሚሰጥ ነገር ነው። በዚህ አጋጣሚ ህብረተሰቡ ደም መለገስ የሰዎችን ህይወት መታደግ መሆኑ ብቻ ሳይሆን ለጤና የሚሰጠው ጥቅም እንዳለ በማወቅ ደም እንዲለግስ እና ብዙ ህይወቶችን እንዲታደግ እጠይቃለሁ። በየቀኑ በደም እጦት ምክንያት እናቶች እና ህፃናት በጣም በሚያሳዝን ሁኔታ ህይወታቸውን ሲያጡ ማየት በጣም አሳዛኝ ነገር ነው። ደም በመለገስ ግን እናቶችን፣ ወንድም እና እህቶቻችንን ማትረፍ እንችላለን። ሌላ ደግሞ በመንፈሳዊ ህይወት እሳተፋለሁ፤ ከዚህ ደግሞ ትልቅ ሰላም እና የመንፈስ መረጋጋትን አግኝቼበታለሁ።

ናይል፡- ለሴት ተማሪዎች በራሳቸው እንዲተማመኑና እንዲበረታቱ ምን ትመክሪያለሽ?

ዶ/ር አክብረት፡- ሴቶች "እንችላለን" የሚል ወኔ ሊኖራቸው ይገባል። ብዙ ፈተናዎች ቢኖርብንም ጊዜ ለሁሉም መልስ ነውና ተስፋ ሳንቆርጥ ማድረግ ያለብንን ነገር ማድረግ አለብን። አንዳንዴ ነገሮች ሁሉ ጨለማ ቢሆኑብንም ሁሉንም በትዕግስት ማሳለፍ እና በአላማችን ፀንተን የምንፈልገው ቦታ ለመድረስ መጣር አለብን።

ናይል፡- በዩኒቨርስቲው ውስጥ ተማሪ ሆነሽ ቆይተሽ አሁን ደግሞ በመምህርነት ቅጥር እየፈፀምሽ ነው። በዚህ ጉዳይ ላይ የተሰማሽን ስሜት ብትገልጭልን? ለወደፊትስ ለዩኒቨርስቲው ምን አስተዋፅኦ አበረክታለሁ ትያለሽ?

ዶ/ር አክብረት፡- ከተማሪነት ወደ መምህርት በመምጣቴ በጣም ደስተኛ ነኝ። በሙያዬ ብዙ ነገር እሰራበታለሁ ብዬ አስባለሁ። ለዩኒቨርስቲውም የምችለውን ሁሉ በማድረግ መልካም ፍሬ ያለው ተማሪ በማፍራቱ በኩል ያላሰለሰ ጥረት አደርጋለሁ፤ እንዲሁም የታካሚዎቼን ደህንነት በመጠበቅና መልካም አርአያ በመሆን የምችለውን ሁሉ በመስራት ለዩኒቨርስቲው መልካም ስም ጉልህ አስተዋፅኦ አበረክታለሁ።

ናይል፡- ሌሎች ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ የምታስተላልፊው መልእክት ካለ እድሉን እንስጥሽ?

ዶ/ር አክብረት፡- አንድ ሰው ወይም ተማሪ የራሱ የሆነ የአጠናን ዘዴ ሊኖረው ይገባል። ይህን ያልኩበት ምክንያት ለአንዱ የሚሰራው ዘዴ ለሌላው ስለማይሰራ ነው። በእርግጥ ካምፓስ ውስጥ ብዙ ጭንቀት /ቴንሽን/ ቢኖርም በአግባቡ ጊዜን መጠቀም እና በቂ እረፍት አድርጐ ለሚቀጥለው ቀን መዘጋጀት እንዲሁም በራሱ የአኗኗር ዘዴ መኖር ስኬታማ ያደርጋል ብዬ አስባለሁ። በተጨማሪም ትልቁ የስኬት ሚስጥር ብዬ የማስበው ትዕግስት እና የመንፈስ ጥንካሬ ይዞ ለአላማ መፅናት ነው።

ናይል፡- ጊዜሽን መስዋዕት አድርገሽ ለናይል አንባቢዎች ልምድሽን ስላካፈልሽ እናመሰግናለን።

ዶ/ር አክብረት፡- እኔም እንግዳችሁ አድርጋችሁ ስለጋበዛችሁኝ በጣም አመሰግናለሁ።

# Graduation of Medical Doctors in Pictures







Class of 2016

# ፍናፍንት ምእራፍ ሁለት

በታምሩ ከፈለኝ (የሻረግ)
(www.facebook.com/ደቀ ከፈለኝ ወየሻረግ)
የ3ኛ አመት የኢትዮጵያ ቋንቋ(ዎች) እና ስነፅሁፍ ትምህርት ክፍል ተማሪ

መሰረትና የሹሜ በሸዋንግዛው መሪነት ካጤዳስ የገሰገሱ መንጥቅ ገቡ፡፡ የሹሜ በየመንገዱ ላይ እንደተወጋ አውሬ ድንገት እያጓራች እልህ የምታረገውን እያሳጣት፤ ጥቃት እያንገበገባት ትከተል ነበር እንጂ የት እንደምትሄድ አታውቅም፡፡

መሰረት ከመሃል ሜዳ ወደ አዲስ አበባ የሚወስደውን ጥርጊያ መንገድ ሲሻገር የሚሄዱበትን ሳያውቅ ዝም ብሎ መከተሉ ስላስጨቀው ሸዋንግዛውን ወዴት እንደሚሄዱ ጠየቀው፡፡ ሸዋንግዛው ግን ልቡ ቀድሞ ያረፈው መንጥቅ ነበር ደመኛው ቤት፡፡

መሰረት መልስ ሲያጣ ድጋሚ ጠየቀ፡፡ "ሰዎቹን አውቀሃቸዋል እንዴ ሸዋ?" የሹሜም ጆሮዋ ቆሞ የሸዋንግዛውን መልስ ትጠብቅ ጀመር፡፡ እሷም ሸዋንግዛውን ትከተል እንጂ ወዴት እንደሚሄዱ አታውቅም ነበር፡፡ ብቻ ግን በልቧ አንድ ነገር አለ፡፡ አቅፎ ያሳደጋትን ያሳደገችው የቆጨውን) ገዳይ መግደል፡፡ ለዚህም ነበር በዕልህ እየተወራጨች ሸዋንግዛውን ስትከተል የነበረው፡፡

"መች አጣኋቸው!" ድምፁ ተሰናኩሯል፡፡ እልህና መጠቃት አግለብልቦታል፡፡

"ቀደም ቂም ነበራቸው?"

"እንዲህ የከረረ ስላልመሰለኝ ታገስ ብየው እንጂ እሱስ አይተኙልኝም ሲለኝ ነበር፡፡"

"እነ ማን ናቸው?" የሹሜ ጣልቃ ገባች፡፡ ድምጿ ውስጥ ቁጣ መሸጓል፡፡

"አታውቂያቸውም የሹም"

"ቤታቸውን ታውቀዋለህ?" እንደገና ጠየቀች፡፡

"አዎ!"

"ፍጠኑ እንዳያመልጠን" አለች በግራ እጇ እንደ ዘበት ያንጠለጠለችውን አጭር ምንሽር ወደ ቀኟ እያዞረች፡፡ "ፍጠኑ!"

እስካሁን ከነሱ እኩል ትራመድ የነበረችው አሁን ቀድማቸው ስትገሰግስ በሩጫ ጭምር እየተራመዱ ከኋላዋ ይከተሏት ጀመር፡፡

መንጥቅ ሲደርሱ ጨለማው ላይን ያዝ ማድረግ ጀምሮ ነበር፡፡ ሲገቡ ሸዋንግዛው ቀደም ብሎ እየመራቸው አንድ ብቻዋን ቂጥጥ ያለች ጎጆ ስር ሲደርስ ቆመና ጎጆዋን ይመለከት ጀመር፡፡ ጎጆዋ ከላይ ጉልላት ተቀምጦላታል፡፡ ዙሪዋም በድንጋይ ካብ ታጥሯል፡፡ አጥሩ ከፊት ለፊት እድሞ ተሰርቶለት እኔ ነኝ ያለ በር ተገጥሞለታል፡፡

"እህ!" አለ ሸዋንግዛው ትንሽ ራቅ ብሎ ቆሞ ቤቱ ይሄ ነው በሚል ስሜት በአገጩ ወደ ጎጆዋ እየጠቆመ፡፡ ጎጆዋን ባንድ ጥይት አንድዷት ከሳት ተርፈው የሚወጡትን ሰዎችን ከዳር ቆሞ በጥይት ሊለቅማቸው ከጅሏል፡፡

"ይሄ ነው ቤቱ?"

"አዎ" መለሰ

"እንዴ. . . ይሄ የጌታቸው ልጅ ቤት አይደል እንዴ?" የሹሜ ጠየቀች፡፡

"አዎ"

"እሱ ነው ወንድሜን የገደለው? እሱ ነው ቀኝ እጄን ቆርጦ ዱሽ ሊያረገኝ ታጥቆ የተነሳው? አይ ሱሪ! አይ ወንድ! አውነትም ሱሪ ታጥቋልና፡፡ በጄ በልቶ በጄ ጠጥቶ ጉድ ያርገኝ?" አለች ለጥር ባለወልድ መጥቶ ቤቷ ያስተናገደችውን እያሰበች፡፡

ጊዜ ሳትፈጅ መሳሪያዋን አቀባብላ በጠበቂያ ከፍታ ወደ ጎጆው ክዳን ስታነጣጥር መሰረት በፍጥነት አፈሙዙን ያዘባትና ቀና አደረገው፡፡ የሷን አፈሙዝ ቀና አድርጎ እንደያዘው ሌላ የሚቀባበል መሳሪያ ድምፅ ሰምቶ ዞር ሲል ሸዋንግዛው የክላሹን መጠበቂያ ከፍቶ ጎጆዋ ላይ ሲያነጣጥር አየው፡፡ ምንም ነገር ለመናገር ጊዜ ስላልነበረው በቀኝ እጁ የያዘውን ታጣፊ ክላሽ በማንገቻው በክንዱ አንጠልጥሎ የሱንም አፈሙዝ ቀና አደረገበትና "ጎበዝ ተረጋጉዪ! ረጋ ብለን እንመካከሪ ጎበዝ"

"ምን ምክክር አለው? ዘር ማንዘሩን አነድለታለሁዪ" ሸዋንግዛው ትንፋሹ እንደሳት ላንቃ እየተጋረፈ እልህ እያንቀጠቀጠው ተናገረ፡፡

"የወንድሜን ደም እንዳፈሰሰው እሱንም ላንድደዊ የምን ምክክር ነው?" የሹሜ እየተግለበለበች መለሰች፡፡ ተኩሶ እንደማያውቅ ገበሬ ቃታ መሳብ ናፍቋታል፡፡ የመሳሪያዋን ምላጭ እስኪበቃት ስባ ቤቱ በሳት ሲጋይ ማየት ውል ውል ብሏታል፡፡

"ተው!" አለ መሰረት ተረጋግቶ በሚያረጋጋ ድምፅ፡፡ "የቆጨው ወንድምነት እኮ ለናንተ ብቻ አይደለም፡፡ በስጋ አንዋለድ እንጂ የኔም ወንድሜ ነው፡፡ ስለዚህ ሞቱ ያንገበግበኛል፡፡ ጥቃቱም ጥቃቴ ነው፡፡ እንኳን የሱ ይቅርና ማንም የቀዬ ሰው እንዲህ ባደባባይ ደጁ ክምብል ብሎ ሳይ ልቤ ይበግናል፡፡ ገዳዩን ለህግ ማስረከብ እንዲያም ሲል ደሙን መመለስ ያምረኛል፡፡ ግን እንዲህ ተሁኖ አይደለም ደም የሚመለሰው፡፡"

"እና እንዴት ነው?" ሸዋንግዛው በብሽቀት ጠየቀ፡፡ የመሰረት ስራ ውስጡን እያበሸቀው ነው፡፡ እሱ ሆኖበት እንጂ ሌላ ሰው ቢሆን እስካሁን የሚታገስበት አንጀት የለውም፡፡

"ተረጋጉ! ድንገት ቤቱ አልገባ ከሆነ ይገነግንና ያመልጠናል፡፡ ልጆቹና ሚስቱም በሱ ጥፋት መቀጣት የለባቸውም፡፡ ስለዚህ እኔ ቀስ ብዬ ገብቼ መኖሩን አጣራለሁ፡፡ ከዛ ቅጣታችንን እንቀጥላለን፡፡"

"አንተ ስትገባ ሰምቶ ቢወጣና ተኩስ ከፍቶ ቢያሲዘንስ"

"ማን አባቱ ነው የሚይዘን? ሱሪ ታጥቂያለሁ የሚል መጥቶ ይሞክረኛ!"

"ተው እንደሱ አትበል ሸዋ፡፡" አለ መሰረት ለስለስ ብሎ፡፡ "እእእ ተኩስ ከፍቶ ቢያሲዘን ላልሸው ችግር የለም በኔ ይሁንባችሁ! እናንተ ብቻ እዚህ ጠብቁኝ" ብሎ ወደ በሩ ሄደ፡፡ በሩ ከውስጥ ስለተቀረቀረ ድምፅ ሳያሰማ ለመግባት አልመች አለው፡፡ ከበሩ በስተቀኝ ወዳለው የድንጋይ ካብ አጥር ሲጠጋ አጥሩ ከቁመቱ ዘለል ብሎ ለመዝለል አልመች ብሎት ዞር ሲል ካጥሩ አንድ ሶስት እርምጃ ርቀት ላይ ጉልበቱ አካባቢ የሚደርስ ጉቶ ተመለከተ፡፡

ዞር ዞር ብሎ እነ የሹሜ እንደማያዩት ካረጋገጠ በኋላ ጊዜ ሳያጠፋ ክላሹን በግራ እጁ ይዙ በፍጥነት በቀኝ እጁ ጉቶውን እረገጠና ተፈናጥሮ ወዳጥሩ ዘለለ፡፡ ሰውነቱ ባጥሩ ትክክል ሲሆን አየር ላይ እንዳለ ወደ ግቢ ተገልብጦ ድምፅ ላለማሰማት ተጠንቅቆ መሬት አርፎ በቀኝ እጁ የክላሹን አፈሙዝ ቀና አድርጎ የግራ እጁን አመልካች ጣት ቃታው ላይ አሳርፎ ወደ በሩ አነጣጠረ፡፡ ጥቂት አድፍጦ ቢጠብቅም ድምፅ ሰምቶ ከቤት የወጣ ሰው ባለመኖሩ ወደ በሩ እያደባ ሄደ፡፡

የሹሜና ሸዋንግዛው ከውጪ እየተቅበጠበጡ ቆመዋል፡፡ የሹሜ ሰውነቷ ሁሉ እንደ ትኩስ ስጋ ይንቀጠቀጣል፡፡ አሁንም አሁንም እንባዋ ባይኗ እየሞላ ቢያስቸግራትም ላለማልቀስ ከራሷ ጋር ትግል ጀምራለች፡፡ ሸዋንግዛው አንድ ቦታ ረግቶ መቆም ተስኖት ይንጎራደዳል፡፡ ለወንድሙ ሞት ራሱን ተጠያቂ አድርጎታል፡፡ በልቡ "ምነው ያኔ የነገረኝ ጊዜ ሳይቀድሙኝ በቀደምኳቸው" እያለ ነው፡፡

በድንገት ከውስጥ በኩል በር ተከፈተ፡፡ በተከፈተውም በር አንድ ሰው መሰስ ብሎ ወጣ፡፡

የሹሜና ሸዋንግዛው ገና የበር መከፈት ድምፅ ሲሰሙ መሳሪያቸውን አቀባብለው አነጣጠሩ፡፡ የሹሜ ግራ እግሯን ወደፊት አስቀድማ ከጉልበቷ አጠፍ አድርጋዋለች፡፡ የቀኝ «አግሯን ወደ ኋላ አድርጋ ትንሽ ሸብረክ አድርጋዋለች፡፡ መሳሪያዋንም በቀኝ እጇ ቃታ ይዛ በግራ እጇ አፈሙዙን አስተካክላ ሰደፉን ትከሻዋ ላይ ለግዳ ይዛ ግራ አይኗን ጨፍና በቀኙ አልማ ከተከፈተው በር ውስጥ በወጣው ሰው ግንባር ላይ አነጣጥራለች፡፡

ሸዋንግዛውም እንደሷው ተዘጋጅቶ ሰውዬው ላይ አነጣጥሯል፡፡

በድንገት ሁለቱም መሳሪያቸውን ከትከሻቸው ነጠቅ አድርገው የተመካከሩ ይመስል በቀኝ እጃቸው አፈሙዙን እየዘቀዘቁ አንጠለጠሉት፡፡

"እ?" አለ ሸዋንግዛው በየት እንደገባ ባያውቅም ከተከፈተው በር የወጣው መሰረት መሆኑን ሲያረጋግጥ፡፡

መሰረት ወደነሱ ተጠግቶ "በቤቱ ውስጥ ማንም የለ፡፡ የሰው ድምፅ አይሰማም፤ ላምባም አልተለኮሰ፡፡" ከማለቱ የሹሜ "ታዲያ እኔ ቤቱን እለኩስለት የለ እንዴ!" ብላ መሳሪያዋን ቀና አድርጋ ተኩሳ የጎጆውን የሳር ክዳን መታችው፡፡ ሸዋንግዛውም ደገመው፡፡

ገና በመጀመሪያው ጥይት ከግራ በኩል ቢል ብሎ የነደደው ጎጆ በሁለተኛው ጥይት ደግሞ ከቀኝ በኩል ተንቦገቦገ፡፡ የሹሜና ሸዋንግዛው እየተቀባበሉ ሁለት ሁለት ጥይት ተኩሰው በሚንቀለቀለው እሳት ላይ አሳት ጨመሩበት፡፡ መሰረት ተው ሊላቸው ቢከጅልም እንዲህ ካላደረጉ እልሃቸው እንደማይበርድ ስለገባው ዝም ማለትን መርጦ ከኋላ ሌላ ሰው እንዳይመጣ ዙሪያውን በንቃት ይጠብቅ ጀመር፡፡

የእሳቱ ነበልባል አካባቢውን ወጋገን ስላደረገው የጥይት ድምፅ ሰምቶ ከቤቱ የሚወጣው ሰው እንዳያያቸው ሶስቱም አጎንብሰው ወደ መሃልሜዳ የሚወስደውን መንገድ ይዘው እየሮጡ ሄዱና ካንድ ሸጥ ውስጥ ተደበቁ፡፡ እነሱ ከተደበቁበት ሸጥ ጀርባ የርሻ መሬት እንጂ መንደር ስለሌለ ማንም ከኋላቸው እንደማይመጣ ገምተዋል፡፡

ከላይኛው መንደር ግን ሰዎች ብቅ እያሉ የሚነደውን ቤት እየተመለከቱ ሴቶች ሉሉሉታውን እያቀለጡት ወጡ፡፡ ወንዶቹ ወደቤታቸው እየተመለሱ ያለወ ጠብመንጃ የሌለው ጭስ የጠገበ ከዘራውን እየመዠረጠ ወደሚንቀለቀለው ቤት ጀመር፡፡

ከየቤታቸው የወጡት ሰዎች የባልደረባቸውን ቤት ከሳት ለመታደግ

> መሰረት እንደገባ አንድ ጥግ ይዞ ተቀምጦ ይንሰቀሰቅ ጀመር፡፡ ለተመልካች አንድ ማህፀን አብሮት የተኛ የአንድ አብራክ ክፋይ ወንድሙ የሞተበት እንጂ ባዳ የሞተበት አይመስልም፡፡

ባካባቢያቸው ካለው ጫካ የባህር ዛፍ ቅጠል እየቆረጡም ሆነ ከምንጭ እየቀዱ ባመጡት ውሃ እሳቱን ለማጥፋት ቢሞክሩም አልችል አሉ፡፡ ሁሉም ይይዙት ይጨብጡት ጠፍቷቸው ይዋከቡ ጀመር፡፡

"አር ሰው ውስጥ እንዳይኖር ጎበዝ!"

"እንደው ማነው ጉድ የሰራን?"

"አረ ነግ በኔ ነው ጎበዝ!"

"ኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡኡ. . . ኡኡኡኡኡኡኡ"

"እሪሪሪሪሪሪሪሪ. . . አ - ረ . . . የ - ጎ - በ - ዝ - ያ - ለ - ህ!"

እነመሰረት ቤቱ ነዶ ሲያልቅ ሰው እንዳያያቸው ከገቡበት ጥሻ በልባቸው እየተሳቡ ወጥተው ቁልቁል ከሄዱ በኋላ በሽረሽር በኩል አድርገው ወደ አጤዳስ

ወደ ገጽ 11 ዞሯል

# ለበላይ አካላት ...

ክገጽ 6 የዞረ

በመሆኑ ይዛችሁልኝ ኑ እያለ አዳሜ የሚያስቸግረን አንሶ በሃሜት ጠብሶ ሊበላን ነው!›› እያለ ሲናገር ቆይቶ ሳያሰናብቱት በራሱ ተነስቶ በሩን ከፍቶ ወጣ፡፡

ቀጣይ ቅሬታ አቅራቢዋ ገብታ እንደተቀመጠች ‹‹ያለሽን ሃሳብ መቀጠል ትችያለሽ›› ስትባል ‹‹እሺ አመሰግናለሁ፤ በዚህ መስሪያ ቤት ከተቀጠርኩ በቅርብ ጊዜ ቢሆንም ተቋሙ በዋናነት ለሚያከነውናቸው የተለያዩ የሥራ ዘርፎች ዋና ኤክስፐርት (ሞያተኛ) ነኝ በእርግጥ የሚከፈለኝ በሞያዬ በመሆኑ በመስሪያ ቤቱ ከፍተኛ የመጨረሻው ተከፋይ መሆኔን መግለጥ እወዳለሁ፡፡ ያም ሆኖ አሁን እየተከፈለኝ ያለው ክፍያዬ ከኑሮ ሁኔታው ጋር ሲታዬ የሚመጣጠን አይደለም፡፡ እንደውም በያዝኩት ሞያና የሥራ ልምዴ በNGOና በግል ድርጅቶች ብቀጠርበት ሶስትና አራት እጥፍ እንደማገኝ እርግጠኛ ነኝ፡፡ ስለሆነም መንግስት የሞያተኛው ደሞዝ ያስተካክል የሚል ሃሳብ አለኝ›› አለችና ዝም ስትል ‹‹ለመሆኑ መስሪያ ቤቱ በአሁኑ ወቅት ምን ያህል ይከፈልሻል?›› የሚል ጥያቄ ሲቀርብላት ‹‹ማለት ያው…ው… በግል ድርጅትና በNGO ብቀጠር ኖሮ ከዚህ የበለጠ እንደማገኝ ገልጫለሁ፡፡ ከዚህ ጋር ሲነፃፀር አሁን መስሪያ ቤቱ እየከፈለኝ ያለው ትንሽ የሚባል ነው›› አለች በራስ መተማመን መንፈስ ተሞልታ፡፡ ‹‹እኮ ምን ያህል ገቢ እያገኘሽ ነው›› አሏት በስተግራ በኩል የተቀመጡት ቅሬታ ተቀባይ፡፡ ትንሽ እንደማሰላሰል አለችና ‹‹ምኑም ምኑም ተጨማምሮበት አንድ ሃያ ሺ ብር ይከፈለኛል›› እንዳለች ማህል ላይ የተቀመጡት ሰው እንደ መቁነጥነጥ አደረጋቸውና ለመሳል ሞከሩ፡፡ የጠራችውን የገንዘብ መጠን ከራሳቸው የወር ደሞዝ ጋር ሲያነፃፅሩት እንደ ቅናት ነገር አደረጋቸውና ‹‹እሺ አንቺም እንግዲህ እንደ ሌላው የመስሪያ ቤቱ ሰራተኞች ደሞዝ አንሶኛልና ይጨመርልኝ እያለሽ ነው አይደል?›› አሏት መነጽራቸውን እያስተከከሉና በማስታወሻ ደብተራቸው ላይ እየፃፉ፡፡ ‹‹አዎ ምን ይደረግ ወጫችን ብዙ ነው!›› ስትል ‹‹እሺ ቅሬታሽን ተቀብለናል›› እንደተባለች ተነስታ እንደወጣች ሶስቱም ቅሬታ ሰሚዎች እኩል እርስ በርሳቸው ተያዩ…

የበላይ አካላት የተባሉት ቅሬታና ጥቆማ ሰሚዎች እንዲህ ባለ መልኩ የሰራተኛውን ሃሳብ ሲያደምጡ ውለው ተመሳሳይና አንድ አይነት ቅሬታ መሆኑን ቢገነዘቡም ምንአልባት የተለየ ይኖር ይሆናል ብለው በመገመት በፅሁፋ የቀረበላቸውን ጉዳይ ፖስታዎችን እየቀደዱ ማየት ሲጀምሩ ‹‹እኔ በመስሪያ ቤቱ ውስጥ በፀሃፊነት የማገልገል ሠራተኛ ነኝ፡፡ ስራዬና ክፍያዬ ስለማይመጣጠን ደሞወዝ መንግስት እንዲጨመር አመለክታለሁ፡፡›› ይላል የመጀመሪያው ሃሳብ ‹‹ያው ነው›› አሉ ያነበቡት ሰው፡፡ ይቅሬታ ሰሚዎች አስተባባሪ የሆኑት ሰው እጃቸው ላይ የገባውን አንድ ፖስታ ከፍተው ማንበብ ጀመሩ ለባልደረቦቻቸው በሚሰማ መልኩ ነበር የሚያነቡት አንብበው እንደጨረሱ ‹‹እንግዲህ የመስሪያ ቤቱ ሃላፊም ሃሳብ ደሞዝ ይጨመርልኝ ከሆነ ሌላውን ወረቀት እየገለጥን ማየት የሚጠበቅብን አይመስለኝምና ፖስታዎችን እንዳለ በቦርሳዎቻችን ከተን ብንሄድ ይሻላል›› አሉና በያዙት ጥቁር ቦርሳ ከፊት ለፊታቸው ከተቆለሉት ፖስታዎች መክተት ሲጀምሩ ቀሪዎችም እንደ እርሳቸው ማድረግ ጀመሩ፡፡

ከጊዜያአዊ ቢሮአቸው እንደወጡ በመስሪያ ቤቱ ግቢ ውስጥ ሠራተኛው ተሰብስቦ የእነርሱን ምላሽ እንደሚጠብቅ ስለተረዱ በቀጥታ ወደ ተሰብሳቢው ብሶተኛ ፊት ቀርበው ከመካከላቸው አንዱ ቅሬታ ሲቀበል የዋለው ሰው ‹‹እንግዲህ በዚህ መስሪያ ቤት ውስጥ ያለውን አጠቃላይ ችግር አጣርተን መፍትሄ ለመስጠት መምጣታችን ይታወቃል፡፡ በመሆኑም ሰራተኛው ያለውን ቅሬታና ጥቆማዎችን ለማወቅ ባደረግነው ሥራ በፁሁፍም ሆነ በአካል እንዳቀረባችሁት በመስሪያ ቤቱ ውስጥ ምንም አይነት የአሰራር ስርዓት ችግርና አስተዳደራዊ ጉድለቶች አልቀረቡም፡፡ ይሁን እንጂ የሠራተኛው ዋነኛ ጥያቄና ጥቆማው የደሞዝ አንሶኛል ይጨመርልኝ ስለሆነ እኛም የችግሩን አሳሳቢነት በሚገባ ስለተገነዘብን የሰራተኛው ጥያቄ ተገቢውን ምላሽ እንዲያገኝ ቅሬታዎቻችሁን ለበላይ አካላት በሪፖርት መልክ እንደምናቀርብላችሁ ቃል እንገባለን›› በማለት ንግግራቸውን እንደጨረሱ የተሰበሰበው ቅሬታ አቅራቢ ሰራተኛ በአንድ ላይ አጨበጨበ፡፡

የበላይ አካላት የተባሉት ሰዎች የሠራተኛውን ቅሬታ ይዘው ለበላይ አካል ሊያቀረቡ በመጡበት መኪና ተመልሰው እንደሄዱ ወሎ ሳያድር በመስሪያ ቤቱ ሠራተኞች መካከል አንድ ወሬ ጎልቶ ይወራ ጀመር፡፡ ‹‹ስማ እስቲ ሰምተሃል?›› ሲል አንደኛው ‹‹ምንድን ነው እርሱ? አልሰማሁም›› አለ ሌላኛው፡፡ ‹‹መንግስት ለሰራተኛው 80 ፐርሰንት ደሞዝ ሊጨምር ነው እየተባለ ኮ ነው›› ‹‹እንዴት አወቅህ? ማለቴ እንዴት ሰማኸው?›› ይላል በልቡ ደስ እያለው፡፡ ‹‹ጉዳዩ ለበላይ አካላት ቀርቦ እየተወያዩበት ነው አሉ!›› እንደዚህ የተጀመረው ወሬ የአብዛኛውን ቀልብ ገዝቶ ልብን እያስደሰተ አንዳንዶችም አሁን ባላቸው ደሞወዝ ላይ ምን ያህል እንደሚጨምርላቸው በተወራው ጭማሪ ፐርሰንት በየቢሮአቸው ባሉት የሂሳብ ማሽኖች ላይ ሲያባዙ ሲያካፍሉና ሲደምሩ ታይተዋል፡፡

‹‹ሄሎ ሄሎ ባለፈው ከምናስረክበት ዋጋ 20 ፐርሰንት ጨምረህ አስረክብ›› አለ አንድ ጅምላ አከፋፋይ ነጋዴ፡፡ ‹‹ምነው? ምን ተገኘ? የምርት እጥረት አጋጠመን?›› ሲል ሌላኛው ጅምላ አከፋፋይ ነጋዴ ‹‹አልሰማህም እንዴ መንግስት ለሠራተኛው የደሞዝ ጭማሬ ሊያደርግ ነው እየተባለ ይወራል ኮ›› ሲለው ‹‹በጣም ጥሩ እሺ ይጨመራል›› አለና ስልኩን ዘግቶ ‹‹Yes›› አለ በደስታ፡፡

ከጥቂት ሳምንታት በኋላ በአንዳንድ የመንግስት ሠራተኞች ፊት ላይ ቁዘማና ሀዘኔታ ይሰተዋል ጀመር በየ ሻይ ቤቱ በእረፍት ሰበብ እየተሰባሰቡ የምሬት ወሬዎችን ማውራት ተጀመረ፡፡ ‹‹ደረቅ እንጀራ እንኳን ዋጋ ጨመረ ኮ!›› ሲል አንድ ወንደላጤ ሰራተኛ ‹‹ዛሬ ጠዋት የቤት ኪራይ መጨመራቸውን አከራዩቼ ሲነግሩኝ ደነገጥኩ›› አለች ሌላዋ፡፡ ‹‹ይገርማችኋል! ትናንት ማታ እቤት እንደገባሁ ትንሹ ልጄ አንድ ወረቀት ሰጠኝና ሳነበው የሚማርበት የግል ትምህርት ቤት ክፍያ እንደጨመሩ የሚገልጥ ደብዳቤ ነበር፡፡›› አለ ሌላውም ‹‹ኸረ ተውን እስቲ አሁንስ ባሰበው ባሰበው ታከተኝ ሰሞኑን ምን ያልጨመረ ነገር አለና ነው፡፡ ምን አልባት ያልጨመረ ነገር አለ ከተባለም ሠራተኛው ለበላይ አካላት ያቀረበው የደሞዝ ጭማሬ ብቻ ነው!›› እየተባለ ተወራ፡፡

ᘓᘓᘓᘓᘓ

# ፍናፍንት ...

ክገጽ 10 የዞረ

ገሰገሱ፡፡

አጤዳስ ሲገቡ እሬሳ ቤት ገብቶ ያካባቢው ሰው ተሰብስቦ ቤተሰብ እያስተዛዘነ ደረሱ፡፡ ሁሉም ሽዋንግዛውንና የሹሜን ያለቅሳሉ ብሎ አይን አይናቸውን ቢያይ እነሱ ግን ካይናቸው ጠብ ያለ እንባ አልነበረም፡፡ ሁለቱም ያገኘውን ሁሉ እንደሚበላ እሳት እየተግለበለቡ ይንቆራጠጡ ጀመር፡፡

መሰረት እንደገባ አንድ ጥግ ይዞ ተቀምጦ ይንሰቀሰቅ ጀመር፡፡ ለተመልካች አንድ ማህፀን አብሮት የተኛ የአንድ አብራክ ክፋይ ወንድሙ የሞተበት እንጂ ባዳ የሞተበት አይመስልም፡፡ የመሰረትን ለቅሶ ሲያዩ እንደባህሉ ሊቀበሉት ውስጥ ያሉ ሰዎች እዬዬ ማለት ቢጀምሩም የየሹሜና የሸዋንግዛው አለማልቀስ ስላስገረማቸው እነሱን አፍጠው ሲመለከቱ መሰረትን እረሱት፡፡ መሰረት ግን አልተቀበሉኝም ብሎ ማንንም ሳይቀየም ብቻውን መንሰቅሰቁን ቀጠለ፡፡

የሹሜ እልህ እየሰበቃት መሳሪያዋን በግራ እጇ እንደያዘች የቀኝ እጇን አመልካች ጣት ጆሮዋ ውስጥ ወትፋ ሽላሎውን በረጅሙ ትሰነጥረው ጀመር፡፡

“ጀግና በሉት ሰዎች ወንድሜን ገሎታል

ጎበዝ በሉት ሰዎች ትንሹን ገሎታል

ያለርሱ እይሆን ብሎ የኔም ልቤ ቆሟል፡፡

ወንድሙን ሲገሉት ወንድሙ ካልከፋው

ወንድሙን ሲገሉት ወንድሙን ካልከፋው

አቅርቡለት ልብሱን ደሙ እንዲከረፋው፡፡”

ሸዋን ግዛው “ዘራፍ!” ብሎ የክለሹን ሰደፍ ከመሬት ለገደው፡፡

“ዘራፍ አካኪ ዘራፍ!

የወንዶቹ ዘር የሁሉ ጌታ

አሻግሮ መቺ ቆላ ከደጋ

እጥፍጥፍ ያለው እንደ ነጠላ

አተኳኮሱ በድንጋይ ጥላ

በዚህም ወጣ በዛም ወረደ

ጥይት እንደሳት እያነደደ” ብሎ ሲፎክር የሹሜም ትፎክር ጀመር፡፡

ንስሃ አባታቸው መምሬ ቀለመወርቅ ተነስተው ሁለቱንም ተቆጥተው እንዲቀመጡ አደረጓቸው፡፡ ሁለቱም ተቀምጠው የመሳሪያቸውን ሰደፍ መሬት እያስነኩ አፈሙዙን ተደግፈው ይንሰቀሰቁ ጀመር፡፡ የተሰበሰበው ሁሉ እነሱን ሲያይ ለቅሶውን እንደገና ጀመረ፡፡ ሁሉም ያለቅስ ጀመር፡፡

ይቀጥላል. . .

መታሰቢያነቱ ያልገባቸው ኩስ እንደነካው ለበቅ ወዲያ ላሽቀነጠሩት ለደራሲ ዳኛቸው ወርቁ፤ እንዲሁም ሞተው ሳለ ህያዋንን (እኔን መሳይ) ለሚበልጡ ለበአሉ ግርማ፣ ደበበ ሰይፉ፣ ገ/ክርስቶስ ደስታ፣ ሎሬት ፀጋዬ ገ/መድህን፣ ስብሃት ገ/እግዚያብሄር፣ ሀይሉ ገ/ዮሃንስ (ገሞራው)፤ በርግማንህ ውስጥ ምርቃት መኖሩ ሲታወቅ ጉድ ይፈላ ይሆናል!

# ጽ/ቤቱ ለአመራሮች እና መምህራን ...

ክገጽ 5 የዞረ

የዩኒቨርሲቲው ምርምር እና ማህበረሰብ አገልግሎት ም/ፕሬዚደንት ዶ/ር ሙሉነሽ ስልጠና የሰጡትን የህግ፣ የግዥ እና የፋይናንስ ባለሙያዎችን አመስግነው በሥራ ላይ የሚገጥሙ ችግሮች ሥራውን ከመሥራት እና የዩኒቨርሲቲውን ራዕይ እና ተልዕኮ ለማሳካት የመነጨ በመሆኑ ተባብሮ መሥራት እንደሚገባ ገልጸዋል፡፡ በውይይቱ የተነሱትና ከዩኒቨርሲቲው አቅም በላይ የሆኑ ችግሮችን ትምህርት ሚኒስተርም ሆነ ዩኒቨርሲቲዎች በጋራ በመሥራት መቀየር ያለባቸው ፖሊሲዎች ላይ ከፍተኛ ትኩረት መስጠት እንደሚገባው ዶ/ር ሙሉነሽ አሳስበዋል፡፡

የማህበረሰብ አገልግሎት ዳይሬክተር አቶ ዓብይ መንክር መመሪያውን በመከተል እና በመነጋገር አመች የሥራ ሁኔታ በመፍጠር ሥራ መሥራት፣ የመግቢያ ሰነዶች በሚፈረሙ ጊዜ የህግ ባለሙያዎችን ማማከር እንዲሁም የምርምር በጀትን በአግባቡ ለመጠቀም እቅድን በሰአቱ ማስገባት እንዲለመድ አሳስበዋል፡፡

አዋጆች እና መመሪያዎች በተዋረድ ለሁሉም ዩኒቨርሲቲው ማህበረሰብ በማሳወቅ ዩኒቨርሲቲው በ2017 ያቀደውን የምርምር ተቋም የመሆን ራዕይ ለማሳካት ለምርምሩ አመች የሆነ የፋይናንስ እና የግዥ ስርዓት መዘርጋት እንዳለበት ተሳታፊዎች ሃሳብ ሰጥተዋል፡፡

# ተቋሙ ለተመራማሪዎች የአቅም ...

ክገጽ 5 የዞረ

በማቀድና በመተግበር እንዲሁም የተተገበሩት ርምጃዎች ያመጡትን ለውጥ በመገምገም የሚሠሩ መሆናቸውን አስታውሰው ተመራማሪዎች የምርምሩን ሂደት የበለጠ ይገነዘቡት ዘንድ ስልጠናው መታቀዱን ገልፀዋል፡፡

ስልጠናውን የሰጡት በቅርቡ የፒ.ኤች.ዲ ትምህርታቸውን ከቤልጂየም ሀገር ጨርሰው የመጡትና ተቋሙን የተቀላቀሉት ዶ/ር ዳዊት ጥበቡ ሲሆኑ ለዶክትሬት ትምህርታቸው ማሟያ የሠሩት ምርምር በዲዛይን ሪሰርች ሞዴል የተሰራ በመሆኑ ሠልጣኞች ከስልጠናው የሚያገኙትን ተሞክሮ በምርምራቸው ላይ ለመተግበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንደሚኖረው ተገልጿል፡፡ ስልጠናውን የተካፈሉት ሰላሳ ሁለት ተመራማሪዎች ሲሆኑ ከትምህርትና ስነ-ባህርይ ኮሌጅ፣ ከሳይንስ ኮሌጅ እና ከሂውማኒቲስ ፋኩልቲ የተውጣጡ ናቸው፡፡

# About Chinese Tests - HSK Exam

Dr. Zhang Wenxia

HSK exam (Hanyu Shuiping Kaoshi) is international Chinese language ability test that tests and rates Chinese language proficiency. It assesses non-native Chinese speakers' abilities in using the Chinese language in their daily, academic and professional lives on the basis of Chinese Language Proficiency Scales of Other Languages. Chinese Ministry of Education uses HSK test results as the language criterion for foreign students to enroll in degree-granting programs in Chinese universities.

Chinese Language Teaching Center of Confucius Classroom at Bahir Dar University is the exclusive organizing body for HSK exam in Amhara National State Region. So far, there are altogether 170 students and staff registered HSK exam since the Chinese Language Scheme was launched at BDU in March 2014. Above all, those who took part in the exam got excellent marks in every statistical aspect. Two students were selected to go to Beijing for summer camp in July 2016.

In order to make HSK exam understood well and widely, the following is about HSK exam in details, including its questions types and marking criterion and so on.

To help evaluate the Chinese levels of non-native Chinese speakers across the world, the Confucius Institute Headquarters (Hanban) has developed three exams, HSK (Hanyu Shuiping Kaoshi), YCT (youth learner test) and BCT (business Chinese test). We will provide outstanding examinees with scholarships and all of you with opportunity of summer/winter camps.

Up to now, the Chinese testing centers have spread all over domestic and foreign lands. Internationally, there are 180 testing centers in 60 countries. And in 2009, more than 600,000 Chinese learners registered and attended our tests, among which, 436 received scholarships and 333 winter camps.

### Aim and Purpose

• initiating/perfecting a Chinese evaluation system that is practical, motivational and effective, so as to enhance the qualities of Chinese teaching and learning internationally;

• providing Chinese evaluation services that are the most influential and reliable.

### HSK: Chinese Proficiency Test

The new HSK test was launched by Hanban in an effort to better serve Chinese language learners. The test is the result of coordinated efforts by domestic and foreign experts from different disciplines including Chinese language teaching, linguistics, psychology and educational measurement. The new exam combines the advantages of the original HSK while taking into consideration recent trends in Chinese language training by conducting surveys and making use of the latest findings in international language testing.

#### I. Test Structure

The new HSK is an international standardized exam that tests and rates Chinese language proficiency. It consists of six levels, namely the HSK (level I), HSK (level II), HSK (level III), HSK (level IV), HSK (level V), and HSK (level VI).

#### II. Test Levels

The levels of the new HSK correspond to the levels of the Chinese Language Proficiency Scales for Speakers of Other Languages (CLPS) and the Common European Framework of Reference for Languages (CEF) as follows:

| New HSK | Vocabulary | CLPS | CEF |
|---|---|---|---|
| HSK (Level VI) | Over 5,000 | Level V | C2 |
| HSK (Level V) | 2500 | | C1 |
| HSK (Level IV) | 1200 | Level IV | B2 |
| HSK (Level III) | 600 | Level III | B1 |
| HSK (Level II) | 300 | Level II | A2 |
| HSK (Level I) | 150 | Level I | A1 |

Test takers who are able to pass the HSK (Level I) can understand and use very simple Chinese words and phrases, meet basic needs for communication and possess the ability to further their Chinese language studies.

Test takers who are able to pass the HSK (Level II) have an excellent grasp of basic Chinese and can communicate in simple and routine tasks requiring a simple and direct exchange of information on familiar and routine matters.

Test takers who are able to pass the HSK (Level III) can communicate in Chinese at a basic level in their daily, academic and professional lives. They can manage most communication in Chinese when traveling in China.

Test takers who are able to pass the HSK (Level IV) can converse in Chinese on a wide range of topics and are able to communicate fluently with native Chinese speakers.

Test takers who are able to pass the HSK (Level V) can read Chinese newspapers and magazines, enjoy Chinese films and plays, and give a full-length speech in Chinese.

Test takers who are able to pass the HSK (Level VI) can easily comprehend written and spoken information in Chinese and can effectively express themselves in Chinese, both orally and on paper.

#### III. Test Principles

The new HSK follows the principle of "test-teaching correlation", bases the design of the test on the current trends in international Chinese language training, and is closely related to textbooks. The purpose of the test is to "promote training through testing" and "promote learning through testing".

The new HSK emphasizes the objectivity and accuracy of the evaluation and stresses the learners' actual Chinese language abilities.

The new HSK sets clear test objectives to allow the test takers to be able to improve their Chinese language abilities in a systematic and efficient way.

#### IV. Testing Purposes

The new HSK retains the former HSK's orientation as a general (or universal) Chinese language abilities test for adult learners. The results of the test can serve several purposes:

1. A reference for an educational institution's decision-making concerning recruiting students, assigning students to different classes, allowing students to skip certain courses and granting students academic credits.

2. A reference for employers' decision-making concerning the recruitment, training and promotion of test takers.

3. A method for Chinese language learners to assess and improve their proficiency in Chinese.

4. A method for Chinese language training institutions to evaluate training results.

#### V. Results Certificate

Test takers will receive the results for the new HSK issued by Hanban within one month after the test.

### YCT: Youth Chinese Test

The new YCT test was launched by Hanban in an effort to encourage foreign young students to learn Chinese and improve their Chinese language proficiency. As part of this effort, since 2004 Hanban has organized experts from different disciplines such as Chinese language teaching, linguistics, psychology and educational measurement to work on the program, conducting surveys in order to understand the latest trends in overseas Chinese language teaching and learning.

#### I. Test Structure

| Writing Test | Speaking Test |
|---|---|
| YCT (Level IV) | YCT (Intermediate Level) |
| YCT (Level III) | |
| YCT (Level II) | YCT (Beginner Level) |
| YCT (Level I) | |

The new YCT is an international standardized test of Chinese language proficiency. It assesses young foreign students' abilities to use Chinese in their daily and academic lives. The new YCT consists of a writing test and a speaking test, which are independent of each other. The writing test is divided into four levels, namely, the YCT (level I), YCT (level II), YCT (level III), and YCT (level IV). The speaking test is divided into the YCT (Beginner Level) and YCT (Intermediate Level).

#### II. Test Levels

The different levels of the new YCT are similar to some of the levels in the Chinese Language Proficiency Scales for Speakers of Other Languages (CLPS) and the Common European Framework of Reference (CEF); details are as follows:

#### Test

Takers who are able to pass the YCT (Level I) can understand and use some of the most common Chinese phrases and sentences and possess the ability to further their Chinese language studies.

Continued on page 13

# About Chinese Tests ...

continued from page 12

| New HSK | Vocabulary | CLPS | CEF |
|---|---|---|---|
| HSK (Level VI) | Over 5,000 | Level V | C2 |
| HSK (Level V) | 2500 | | C1 |
| HSK (Level IV) | 1200 | Level IV | B2 |
| HSK (Level III) | 600 | Level III | B1 |
| HSK (Level II) | 300 | Level II | A2 |
| HSK (Level I) | 150 | Level I | A1 |

Test takers who are able to pass the YCT (Level II) can understand and use some simple Chinese phrases and sentences and cope with basic level communications.

Test takers who are able to pass the YCT (Level III), having reached an excellent level in basic Chinese, can communicate on familiar daily topics in a simple manner.

Test takers who are able to pass the YCT (Level IV) can communicate in Chinese at a basic level in their daily, academic and professional lives. When travelling in China, they can manage most forms of communication in Chinese.

### III. Test Principles

The new YCT aims to improve Chinese language learners' self-confidence and follows the principle of "test-teaching correlation". It bases the design of the test on current trends in international Chinese language training and is closely related to textbook learning procedures. The purpose of the test is to "promote training through testing" and "promote learning through testing".

### IV. Test Purposes

The YCT is intended for students whose mother tongue is not Chinese. The results of the test can serve various purposes:

1. A method for Chinese language learners to assess and improve their proficiency in Chinese.

2. A reference for Chinese language training in schools.

3. A method for Chinese language training institutions to evaluate training results.

4. A benchmark for students who want to participate in the HSK test.

### V. Results Certificate

Test takers will receive their test results for the new YCT issued by Hanban within three weeks after the test.

### HSKK: Spoken Chinese Proficiency Test

Spoken Chinese Proficiency Test HSKK is mainly to test the examinees' Chinese oral expression ability, including HSKK (elementary), HSKK (intermediate) and HSKK (advanced). Voice recording is used in the exam.

### I HSKK Examinees

HSKK (elementary) is primarily for those students who take 2-3 weekly classes for one or two semester and have grasped about 200 most frequently-used words.

HSKK (intermediate) is primarily for those who take 2-3 weekly classes for one to two years and have grasped about 900 frequently-used words.

HSKK (advanced) is primarily for those who take 2-3 weekly classes for more than two years and have grasped about 3,000 frequently-used words.

### II HSKK Examination Levels

The corresponding relationship between HSKK and the Chinese Proficiency Test HSK and the International Chinese Ability Standard is shown in the following table:

| HSKK | HSK | International Chinese Ability Standard |
|---|---|---|
| Advanced | HSK level 6 | Level 5 |
| | HSK level 5 | |
| Intermediate | HSK level 4 | Level 4 |
| | HSK level 3 | Level 3 |
| Elementary | HSK level 2 | Level 2 |
| | HSK level 1 | Level 1 |

HSKK (elementary) examinees can understand and use spoken Chinese to express daily topics and meet the basic communication needs.

HSKK (intermediate) examinees can understand and exchange with the native Chinese speakers.

HSKK (advanced) examinees can understand and express their views fluently in Chinese.

III HSKK Examination Questions

**HSKK (elementary)** is composed of three parts, with a total of 27 questions. The exam lasts about 20 minutes, including 7 minutes for preparation time.

The first part is "listen and repeat", 15 sentences in total. Each sentence is played twice. Repeat the sentence after listening. This part is about 6 minutes.

The second part is "listen and answer", 10 questions in total. Each question is played twice. Answer the question briefly after listening. This part is about 4 minutes.

The third part is "answer questions", 2 questions in total. The two questions are printed on the test paper with Pinyin. Answer the questions with no less than 5 sentences. This part is about 3 minutes.

**HSKK (intermediate)** is divided into three parts, with a total of 14 questions. The exam lasts about 23 minutes, including 10 minutes for preparation time.

The first part is "listen and repeat", 10 sentences in total. Each sentence is played twice. Repeat the sentence after listening. This part is about 5 minutes.

The second part is "talk about pictures", 2 questions in total. Each question is provided with a picture. The examinees talk about the two pictures in an oral passage. This part is about 4 minutes.

The third part is "answer questions", 2 questions in total. The two questions are printed on the test paper with Pinyin. Answer the questions orally. This part is about 4 minutes.

**HSKK (advanced)** is made up of three parts, with a total of 6 questions. The exam lasts about 25 minutes, including 10 minutes for preparation time.

The first part is "listen and restate", 3 passages in total. A passage is played twice. Restate according to the passage heard. This part is about 8 minutes.

The second part is "read aloud", 1 question only. The examinees read the passage printed on the test paper. This part is about 2 minutes.

The third part is "answer questions", 2 questions in total. The two questions are printed on the test paper with Pinyin. Answer the questions orally. This part is about 5 minutes.

### IV. Performance Report

The performance report of HSKK is the authoritative proof of Chinese speaking proficiency. The examinees can log in and check the test result on Chinese Test Service network www.chinesetest.cn. Acquire HSKK report issued by the Confucius Institute Headquarters (Hanban) within a month after the test.

Will continue on next publication

# የአስመራ መንገድ

ቤተልሄም ሃብቴ(ባርካት)
3ኛ አመት
የውጪ ቋንቋዎችና ስነፅሁፍ ት/ክፍል
www.Facebook/betelhem habte

ከተራሮቹ ግርጌ ረጅምና ለጥ ያለ አስፓልት ይታያል፡፡ አቧራና ጭስ የጠገቡ የመኪና ሆድ ዕቃዎች ተኮልኩለው ይገኙበታል፡፡ ስለአስመራ መንገድ ሲወራ የምሰማው ከመንገዱ አስፈሪነትና አስቸጋሪነት ባለፈ ስያሜውን ያወጡለት ጣልያኖች ኢትዮጵያ በነበሩ ጊዜ እንደነበር ይነገራል፡፡ ምናልባትም ድሮ ድሮ አስመራ ከኢትዮጵያ ከተሞች አንዷ ስለነበረች እሷን ለማሰብ የተጠቀሙበት ይሆናል፡፡ አሁን ግን ሁለት መንታ መንገዶችን ከማገናኘት ባለፈ አስመራ ከተማ አያደርስም፡፡

በአስመራ ሰፈር አስፈሪና ጨለማ ነገሮች ይበዛሉ፡፡ ከመንገዱ ማዶ ገነት ተራራ ውስጥ ተሸሽገው የሚኖሩ አራዊቶች ፀሃይ ስትጠልቅ ዋና መንገዱን ይራወጡበታል፡፡ በዛ ላይ የሽፍታው ብዛት እግር ጥሎህ በዛ ስትሄድ ማጅራትህን ብለው እንደካርታ ሜትር መንገዱ ላይ አንጥፈውህ ረግጠውህ ይሄዳሉ፡፡ ቀን ላይ ግን ፀጥ እረጭ ብሎ ይውላል፡፡ ዛሬ ግን ገና በጊዜ ጨላልሟል፡፡ መንገደኛውም ከሩጫ ባልተናነሰ ይጓዛል፡፡ ማርታም ከመንገደኞቹ አንዷ ናት፡፡ በጊዜ መምሸቱ ስላስፈራት ቁና ቁና እየተነፈሰች መሮጥ ጀመረች፡፡ በዛላይ የለበሰችው ነጠላ ግራና ቀኝ ንፋሱ ሲያወዛውዘው አንዴ ፊቷን ሌላ ጊዜ እግሯን እየጠለፋት ጉዞዋን አታካች አድርጎታል፡፡

ከአያቷ ቤት ስትወጣ መንገድ ላይ ተከትለው የሰጧትን ትኩስ የሽንብራ ቆሎ በነጠላዋ ቋጥራ ብትይዘውም መዳፏን እያቃጠላት ነው፡፡ እንዲያም ሆኖ ግን እየሮጠች ነው፡፡ ፊርታ አታውቅም፡፡ በፈለገችው መንገድ ተጉዛ ጀግና መሆን ትወዳለች፡፡ ስቃይዋ መድሃኒት የሌላት ህመም የሆነችባትን ህይወት ለመቀየር ትለፋለች፡፡

ዛሬ ግን ደክማለች፤ በጣም ተረብሻለች፤ ወደቤቷ ለመድረስ አሁን የምትሄድበትን ያስመራ መንገድ ጨርሳ በሚገጥሟት ሁለት መንታ መንገዶች ይወሰናል፡፡ ደግነቱ በሁለቱ መንገዶች ትራንስፖርት እንደልብ ነው፡፡

እያላባት ነው. . . የልብ ትርታዋ ጨምሯል፡፡ በዚህ ሰአት ከራሷ ጋር መደማመጥ ከባድ ነው፡፡ ለሰዎች መረበሽ መንስኤው ከተለያየ አቅጣጫ ሊመጣ ይችላል፡፡ ነገር ግን ሁሉም ሰው መጨነቁና መረበሹ አንድ ያደርገዋል፡፡ የመንገዱ ማገባደጃ ወደሆነው ትልቁ አለት ስትደርስ እፎይታ ተሰማት፡፡ አለቱ ላይ ቆም ብላ ሁለቱን መንታ መንገዶች ተመለከተች፡፡ አንደኛው ወደ ቀኝ ሌላኛው ወደ ግራ፡፡

በግራ በኩል ያለው መንገድ በሰዎች መንጋ ተጨናቋል፡፡ የገበያውን ግርግር፣ የህፃናት ለቅሶ፣ የሙዚቃ ቤቶች ጨኸት፣ የመኪናው ጡርንባ . . . ብቻ ትርምስምሱ የወጣበት አለም

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# ማንነትን የሚያዋድቅና ሞራልን ...

ከገጽ 15 የዞረ

ጋር መጥተው መልሰው ወስደው ከመረመሩ በኋላ ነው» አለች መልሳ አስተማሚዋ::

ሲስተር ሲቲና ሀኪሙ በጠቅላላ ሐኪምነት ደረጃ እያለ ከባለቤቷ ጋር የተማረ ሀኪም በመሆኑ «እኔ አነጋግረዋለሁ» ብላ ሄዳ ጠየቀችው «በቃ አንቺ ራስሽ የሙያው ሰው ነሽ:: ዛሬ ከአለባቸው የማህፀን ችግር ሌላ አናታቸው ላይ ብዙ ደም ፈስሷል:: አንጀታቸው ላይ ከባድ ቁስለት አለ ስለዚህ መድሀኒቱን ቤት ወስዳችሁ ስጧቸው:: እንደ እኔ አዲስ አበባ ሆነ ውጭ ባትደክሙ እመክራለሁ መረጃው ይፃፍለትና አዲስ አበባና ውጭ ወስጄ ልሞክር ሳልሽው ትርፉ ድካም ነው:: ተይውና ቤታቸውን ይዛችሁ ሂዱ አላት::

አስታማሚዋ እየሮጠች «በለጥዬ፣ በለጥዬ ጉድ ሆን፣ ጉድ ሆን፣ እያንገረረች ነው ወይኔ ጉዴ!..... «በቃ ተረጋጊ የአንጋረረ ሁሉ አይሞትም «ብለው ሁሉም እየተሯሯጡ ወደ ክፍሉ ሲገቡ ሲሉ በሩ ተዘግቷል:: እየተጨነቁ ቆሙ:: አትክፈቱ በመባላቸው ጭንቀታቸው ጨመረ:: ከተወሰነ ጊዜ በኋላ በሩ ተከፈተ:: ባትተው ሲነቁ ለመነሳት መሞከራቸው ለአደጋ አጋልጧቸው ነበር የተስተካከለላቸው የአንገት መደገፊያ በመንሸራተቱ የመድሀኒቱ መጠን እንዲበዛና በአፍንጫቸው እንዲወስዱ ማድረጊያው ቱቦ ፈሳሹን ጥሶ ጉሮሮአቸው ውስጥ ማስገባቱ ነበር ጭንቀታቸውን የጨመረው አሁን ተስተካክሏል:: ትንሽ ይረፉና ከሁለት ሰአት በኋላ ይወጣሉ እስከዚያው የአልጋና የመድሀኒት ቀሪ ሒሳብ አጠናቅቁ ደህና ናቸው ብላ ሜትሮና ሀኪሙን ተከትላ ወጣች::

ወ/ሮ በለጡ የኩንትራት መኪና ተኮናትራ መጣች:: ወ/ሮ ዘውዴ ከእህታቸው ቤት አርፈው ይሂዱ፤ ተብሎ ከተማ ገብተዋል:: የእህታቸው ጎረቤቶች፣ ወዳጆችና ቤተሰቦች ማድረግ የሚገባቸውን እያደረጉ ወደየቤታቸው ተመልሰዋል:: ወ/ሮ ዘዉዴ ከንጋቱ ሶስት ሰአት ላይ ይህችን አለም ተሰነባብተዉ አረፉ:: ለየወዳጅ ዘመድ ስልክ ተደዋወለ:: ከማዶም እንዲሁ አስከሬኑ ከጥቂት ቤተሰብ ጋር ተጫነ ዘመዶች፤ ሌላ፤ አባዱላ የተባለ ተሽከርካሪ ተከራይተው ተከተሉ:: ከስማዳ ወረዳ ከተማ ወገዳ ከተማ በርካታ ለቀስተኛ ተሰባስቧል:: በከተማዋ ኗሪ የሆነ አንድ ታላቅ ታዋቂ ሰው መሞቱን የአለቃቀሱ ስነ ስርአት ይገልፃል:: በየአቅጣጫው ከየአካባቢው የቀበሌ ገበሬ አስተዳደር የመጡ ለቀስተኞች ጩኸት፣ ኡኡታ፣ ሙሾ በየረድፍ በየረድፉ የደመቀ ነዉ:: ካባ፣ ቀሚስ የደረቡ፣ ዋንጫ የጨበጡ፣ እንዝርት ፈትልና መቋሚያ የያዙ፣ ፎቶ ግርፍ የያዘ ልጁ የልጁ ልጅ፣ እህት፣ ወንድም፣ ባል፣ ቤተአዝማድ ወዳጅ ሐይማኖት ሳይለይበት ለቅሶው ደምቋ በ13 አቅራቢያ ደብሮች የተውጣቱ ካህናት፣ ዲያቆናት፣ መነኮሳት.... ፍትሀተ ፀሎቱን አድርሰው ቀብሩ ተከናወነ::

ለመሆኑ አደጋው እንዴት ነው? በእግዚአብሄር ነው? ወይስ በሰው እጅ ነው? እንዴት ነው ነገሩ? ...አባ መዘመር ጠየቁ:: እረወዲያ ከጠበሉ ወጥተው ከከተማው የልመና እንጀራ ለምደው ሲንከለከሉ መኪናው በልቷቸው ነው:: ሁለት አመት ሙሉ ቤት ዘግተው ሲጠፉስ ምነዋ? የሚል ሃይ ባይ ጠፍቶ ነው እንጂ...... ሲሉ ታዬ ማጫሽ በመቆርቆር ስሜት ተናገሩ ነገሩ ጥፋቱ የሰውየው ነው:: አሉ መልሰው::

ድፍን ሁለት አመት ሚስትየዋን ጠበል እንዴት አድርጎ አስቀመጠ እርሱም በጉዳዩ ተካፋይ ኑሮ ነው እንጂ ለካስ ይኸ በቅርቡ የፈነዳሙ ሀብት ነገሩ ሌላ ኑሯል? አሉ አንዱ በነገሩ የተገረሙት የቅርብ ወዳጃቸው:: ባላንባራስ ወሰኑ ጋረደው::

እህ! እንግዲያ እንዴት ነው? ከዚያ ጥናፋ ታለው ወንድማቸው ጋር ተጋርተው አንድ የናፍጣ ወፍጮ ሞተር ተክለዋል:: መልሶም ከዚሁ ከኛው ከተማ በርካሽ የጥሎ ሂያጅ ቤት በብር 50,000 (ሃምሳ ሺህ ብር) ካሽ አርገው አውጥተው ገዝተዋል:: ከዚሁ መኖሪያ ቤታቸውም የልጅየው የዶክተሩ ውርስ ተብሎ 12 ክፍል ቤት ተሰርቶ ኪራዩ ከሀብታም ኑሮ በላይ ያደረጋቸው! ለካስ የልመና ገንዘብ ነው? ወይ ፈጣሪ አሉ ሌላኛው::

ታዬ ልቅሜ ምነው በሳቸው ብቻ እኮ አይደለም ይኸ ነገር:: ከስማዳ እኮ እነ አያ ብርሌ ሙጩ፣ እነ ትሁኔ አለሙ፣ እነ ፈንታቢል ጠሀይ፣ እነ ጌታቸው ከፈለኝ አዲስ አባና ግረድዋ(ድሬዳዋ) እየሆዱ ለቅዱስ ዮሀንስ የጻጉሜ እሩፋኤል አይደል እየመጡ ለኛ ሁሉ ከንግድ እንደተመለሰ የቢራራ ነጋዴ ስንት ስንት ዓለም (የደስታ ግብዣ) የሚያሳዩን::

እህ ምን ይላሉ? በጋይንት፣ በፎገራና ደራ ወረዳ ሳይቀር እየተሰደደ እየለመነ አይደል ሀገሩ ሁሉ መቼ በስማዳ ብቻ ባለ አራት ወፍጮ፣ ባለ መንጋላም፣120 ዚንጎ እልፍኝ ተአዳራሽ፣ የከብቱ ቤት እረገይ! አሁን አሁንማ ጉረኖ ሙሉ በግና ፍየል፣ ሱቁ እረ ስንቱ ተከተማውስ ባህር ዳር አዲስ አበባ በምኒዮል ብር የሚያወጣ የሚከራይ ቤት ሁሉ ያላቸውና ባንክ ቤት ባለ አደራዎች ሁሉ አሉ አይደል አለ አባ ባይለየኝ ጠሀይ:: ቀድሞ የስማዳ ምስለኔ (ምክትል አስተዳዳሪ )የነበሩት::

እዲያ! እኛም ተሞኝተን ነሙ አሉ አባ ይሁነው በለጠ:: «እረ ጎመን በጤና! ይኸው የሰው መሳቂያ ለመሆን ነው:: በሰው ዓይን ተገርፎ የተገኘው ገንዘብ ምን ጤና ሊሆን ነው? እረ ይቅር! አሉ እማሆይ ጠለል አበጀ::

ለቀስተኛው ከቀብር መልስ ድንኳን ውስጥ ሆኖ ቡና እየተጠጣ እማ ዘውዴ እንዲህ ጥላው ልትሄድ በልመና ለመክበር ያደረገችውን ሁኔታ የመኪናው አደጋ አጋልጧት ሰውነቷ ተበጣጥሶ ተመኪናው መንገድ ላይ የአካሏ ቁርጥራጭ ተለቅሞ ነው አሉ ለምንኩስና ሳትበቃ በጅምር እንዲያ የሆነችው! ብላ የወ/ሮ አልጣሽ እህት ዘነቡ የጉንጯን ሳትጨርስ እንዷ ተቀበለቻትና በጥፊ ያለሽ ወራዳ!፣ ቆርጦ ቀጥል! እኛ አይደለን እንዴ አብረናት ከነምራቷ፣ እህቷና የእህቶቿ ልጆች ጋር እየተቀያየርን ስናስታምማት የሰነበትን፣ ከእግሯ መቀጥቀጥ፣ ከደረቷ መመታትና ከግንባሯ ደም መፍሰስ በስተቀር ምንም የጎደለ አካል የለም:: «ውሽታም ቡሊ!» ብላ ለመማታት ስትገለገል ሁካታው ግርግሩን አባባሰውና ጥቂት ቆይቶ በገላጋይ ብዛት ነገሩ በረድ አለ::

«የሰማውና ተይ ይቅርብሽ፣ ያገር መሰደቢያ ትሆኛለሽ ያለውና ሰውየዋም ይችን ሰው ተይ በሏት በእርጅና ቤታችን አንፍታ ብሎ ቢለፈልፍ የሚሰማው አጥቶ ለመከራ ወደቀ::» አሉ የእማ ዘውዴ ጣውንት:: እመት አደነቁሽ ይፍሩ:: በመሀል አዳዲስ ለቀስተኛ ገባና ለቅሶው ደራ.........::

ለእንግዶች መሸኛና የድንኳን ማፋረሻ ንፍሮ ተነፍሮ ቡናው ከተጠጣ በኃላ ሰንጋ ተጥሎ በሰባት ቀኑ ለቀስተኛው በየመጣበት ተሸኘ:: በአደጋው ሁለት ሰዎች ሲሞቱ ሌሎቹ ተርፈዋል:: በቀላሉ የተረፈው የየኳሳዉ አስናቀ ደግሞ ታክሞና ለአንድ ወር በጀሶ ታስሮ በተመላላሽ ህክምና በመረዳት በሁለት ክራንች ተደግፎ በመንቀሳቀስ ላይ ነው::

ከዚህ ከዚህ በመነሳት ለምን በዘላቂነት ልመናን ለማመናመን የሚጥር ተቋም አይፈጠርም ያሳደጉን የጎረቤት ሰዎች ሳይቀሩ ኑሮ ሲከብዳቸው ለልመና እየተዳረጉ ነው:: በዚያ ላይ በየለቱ የሐይማኖት በዓላትም ይሁን በየወርና የአመት ክብረ በዓላት ቀን ወደ ጊዮርጊስ፣ ሚካኤል፣ ማርያም፣ ተክለሐይማኖት፣ ገብርኤል........ በሮመዳን በአልና በእለተ አርብም በየድርጅቱና ቤተ መስጊድ መስራት የሚችሉ ወጣት ወንዶች፣ ኮረዶችና ጎልማሶች እንዲሁም ጎዳና ተዳዳሪዎችና የቀን ሠራተኞች ሳይቀሩ በልመና ተሰልፈው እያየን አይደለም እንዴ! አሁንማ ልመና ለሁሉም ሰው በአዋጅ የተፈቀደ እስኪመስል ነው.......ርዕስ እያነሱ ያገባናል የሚሉ ሰዎች በአገኙት አጋጣሚ ሁሉ በጉዳዩ መነጋገር ጀምረዋል::

ህብረተሰቡ ምፅዋትን ወጥነት ባለው አንድ ውዳዬ ምፅዋት በመለገስ በአዊና በላሊበላ ያለውን ቅጥ ያጣ ልመና ለማመናመን እየተደረገ ያለውን ጥረት ሊያበረታታው ይገባል:: እስከመቼ መስራት የሚችል ሀይል በጥገኝነትና በልመና ተመስርቶ የሕብረተሰቡና የመንግስት ሸክም ይሆናል? እያሉ ወጣቶችና ሙሁራንም በአገኙት አጋጣሚ ይወያያሉ:: ከውይይቱ መሀል «አብርሃም ለምን ግን አንድ ነገር አንሞክርም» አለ::

ፀሐይ አነሳችና በአዲስ መልክ ከምንጀምር በዚሁ ከተማ አባይ ማዶ እኮ አንድ ልመናን ለማመናመን ተነሳስቶ 50 አረጋውያንን፣ አካል ጉዳተኞችን የከፉ የጤና ችግር ያለባቸውን እየረዳ ያለ የህዝብ አምባ የበጎ አድራጎትና ልማት ድርጅት አለ:: ለምን እርሱን ጎብኝተነው ህጋዊና ዘላቂነት አቅም ያለው ከሆነ አባል ሆነን አናጠናክረውምና አናሳድገውም? አለች እንጂነር ነብዩ በሀሳቡ ተስማማታ «ይህ ድርጊት ትኩረት እንዲያገኝ አብረን እንጥራለን» አለ ::

«ጥሩ ሀሳብ ነው ሳምንት እሁድ እናየዋለን»:: ሲል ክንድዬ አቋረጠውና ሳምንት እሁድ እንኳ የቢኒ ሠርግ አለ:: ለምን የዛሬ 21 ቀን እንዲያውም የፅዋ ማህበራችን ቀን ነው:: ቀደም ብለን ገብተን ጎብኝተነው ከዚያው ላይ አንወያይም ሲል ሁሉም ተስማሙና ተለያዩ::

**ይቀጥላል!**

# የአስመራ መንገድ ...

ከገጽ 13 የዞረ

ሆኗል:: በተቃራኒው አቅጣጫ ባለው መንገድ ጥቂት ሰዎች አንድ ላይ ሆነው ይጓዛሉ:: የተረጋጋና ሰላም የተሞላበት ኑሮ የሚኖሩ ይመስላሉ:: ሁለቱንም ጎዳናዎች ወደቤቷ እንደሚያደርሷት ብታወቅም ልቧ የመረጠው በግራ በኩል ያለውን ነው::

ከቤቷ ማዶ ስትወጣና ስትገባ በርቀት የምትመለከተው “ያ”ን ስሙን የማታውቀው ቦዘኔ ወጣት ለማየት የሚረዳት የግራውን መንገድ ነው:: ቀኑን ሙሉ ድንጋይ ላይ ተዎዝፎ እየዋለ ብርድና ፀሃይ ሲፈራረቅበት ከጊዚያት በኋላ አናቱ ላይ ፀጉር ሳይሆን አረም ማብቀል መጀመሩ የማይቀር ነው::

እሷም የምታውቀው እዚሁ ድንጋይ ላይ ተጎልቶ ሲውል ነው:: ገና ስታየው ልቧ ይቀልጣል:: ለብዙ ጊዚያት እሱን እያሰበች ወቅቶች መጥተዋል፣ ሄደዋል:: ብዙ ነገሮች በጊዚያቸው አልፈዋል:: ነገር ግን ሁሌም እንደጤዛ የማይጠፋ አንድ ነገር አላት:: ያም ቢሆን ለሱ ያላት ፍቅርና ውዴታ ነው:: ዛሬም ለሱ ስትል ግራዋን መርጣለች:: በቆመችበት ከሃሳቧ ያባነናት የሰዎች ኮቴ ስትሰማ ነው:: አጠገቧ እየቀረቧት የመጡት ወጠምሻ ትክሻዎችን ስትመለከት እግሮቿ በቆመችበት ከዷት:: መንቀሳቀስ አቅቷቸው እንደሃውልት ገትረዋት ቀሩ:: ፊት ለፊቷ ብቻ ያሉትን ስትመለከት የኋላዋን ጨለማ እረስተዋለች:: ነገር ግን ከጨለማው ውስጥ በወጡ ወጠምሾች እጅ የተሰነዘሩ ቅቤ የጠገቡ ዱላዎች አናቷ ላይ ሲያርፉባት ተሰማት:: ተንገዳግዳ ስትወድቅ ቁማበት የነበረው ደም የለመደ አለት ፊቷን አጣበቀው:: የፈጣሪ ስጦታ እንደሆኑት እንደሚያምሩት የበርሃ ቴምሮች የሚያበራው ቆዳዋ ሸንብራ ግርፍ የተገረፈ ግድግዳ መሰለ:: አያቷ የሰጧት የሽንብራ ቆሎ አንዴ እንኳ ሳትቀምስለት አለቱ ላይ ተበተነ:: ከጭንቅላቷ የሚፈሰው ደም ፀሃይ ያንቃቃውን አለት አራሰው:: የሰዎችን ነፍስ መቀማት የለመደው ያስመራ መንገድ የማርታንም ህይወት ለወሮበሎች አሳልፎ ሰጠ:: ህይወት እንዴት እንደሚቀየርም ሆነ እንደሚጠፋ አይታወቅም:: “አንዳንዴ ስሄድ አገኙኒት ስመለስ አጣኒት፤” የሚባለው ተረት ለጤዛ ብቻ ሳይሆን እንደማርታ እንደወጡ ለሚቀሩ ሰዎችም ጭምር ነው::

ከየት መጣ ያልተባለው ዝናብ አለቱ ላይ የደረቀውን ደሟን አጣቦ ትቦ ውስጥ ጨመረው::

የሰዎች የህይወት መስመር ሁለት ነው:: ስጋዊና መንፈሳዊ:: ትክክለኛውን የመምረጥ ድርሻ የባለቤቱ ነው:: ከእንግዲህ ያንን ድንጋይ ላይ የሚቀመጥ ባተሌ ወጣት ማን ይመለከተዋል:: አላወቀችውም እንጂ እሱም ቢሆን እሷን ካላየ ፀሃይ አትወጣለትም::

ተጀምረው የሚቀሩ ብዙ ነገሮች አሉ!

# ማንነትን የሚያዋድቅና ሞራልን የሚገድል ንግድ

## (ሃይ ባይ የሌለበት ግብርና ኪሣራ የሌለበት ንግድii)

### ክፍል ሁለት

በመተሳሰብ ክብሩ

የባህር ዳር ከተማ የፈለገ ሕይወት ሪፈራል ሆስፒታል የቀዶ ህክምና ተኝቶ መታከሚያ ሁለቱ ክፍሎችና በረንዳዎቻቸዉ ሳይቀሩ ሰዉ በሰዉ ሆነዋል፡፡ ሁለት አዋቂ ወንዶች ፤አንድ ወጣት ሹፌር ፤አንዲት ወይዘሮና ሁለት ህፃናት ወንዶች ምሽት ላይ በደረሰ የመኪና አደጋ ህክምና ላይ ናቸዉ ፡፡

ሁለት ወጣት ወንድና ሴት ትራፊክ ፖሊሶች ከአንድ ኢንስፔክተር ጋር ሹፌሩንና ቀላል ጉዳት የደረሰበትን አስናቀን ስለ ጉዳቱ ሁኔታ መረጃ ከተቀበሉ በኋላ ወደ ሀኪሙ ዘለቁ፡፡ የራጁ ውጤቶችን ከነመግለጫቸዉ ተረድተዉና የከፋና ቀላል ጉዳት ለደረሰባቸዉ ቁስለኞች ሙያዊ መረጃ ተቀብለው ተመለሱ ፡፡

ወደ አስታማሚዎች ጠጋ ብለዉ አንዷን አስታማሚ በጠና ስለተጎዳዉ ቁስለኛ ጠየቋት፡፡ እኔ ወለል አከራይ ነኝ፡፡ በርግጥ ሲደወልልኝ በርሬ ደረስኩ፡፡ ለዚህ ሰውዬ የቀበሌ መታወቂያ ያወጣሁለት እና የአደጋ ተጠሪውም እኔ ነኝ፡፡ ጥሩልኝ ሲላችሁ ጊዜ አስጠራችሁኝና በርሬ መጣሁ ይኸዉ ማታም ዛሬም ለእህል አልበቃሁም አሁን ግን ቀዶ ህክምና ተደርጎለት ታክሞ ከወጣ ትንሽ ስቃዩ ስለታገሰለትና ስለተኛ ቤቴ ደርሼ ልመጣ ነዉ አለች፡፡

ኢንስፔክተሩ «ትናንት ታማሚው ወደ ቀዶህክምና ሲገባ የፀሎት መፅሐፍ ከነ ከረጃውና የዲሪቶ ድራቡና አልባሳቱን የያዝሽው አንቺ ነበርሽ» ማየት እንችላለን አለ፡፡ «ይኸዉ» አለች፡፡ ኢንስፔክተሩ ለወጣት መርማሪ ፖሊሱ ተቀበላት አለውና ትራፊክ ፖሊሱንና ሌሎች ሶስት ታዛቢዎችን አስቀመጠ፡፡ ሁሉንም ከነሙሉ አድራሻቸዉ መዝግበው እማኝ ባለበት ማህደሩን ከፈቱት፡፡ አንዱ የፀሎት መፅሐፍ ብቻ ነው የያዘው፡፡ ሁለተኛው ግን የ30ሺህ ብሮችን በላስቲክና በጨርቅ ሸፍኖ የተጠረዘ ነዉ፡፡ ቀጠለና ዱርቶውን አስነሳ፡፡ ደሪቶው ሲነሳ ከብዷል በቁርጥ በቁርጥ በአራት ድራብ ጨርቅ በሁለት ገፅ የፕላስቲክ ሸራ፣ በመሀል፣ አብጄዲ ጨርቅና መልሶ ፕላስቲክና እራፊ ጨርቆች ተጀብኖ በዝሃና በሲር ክር በጥንቃቄ በየስንዝሩ ርቀት በአራት ማዕዘን የተሰፋ ነዉ፡፡

በእያንዳንዱ የስፌት ማዕዘን ዉስጥ አደጋ የደረሰበቱ ለምኖ አዳሪ አዛናው ይልቃል የአበደረበት የውል ሰነድና የብር ኖት ተጠቅልሎ አራት ቦታ አገኙ ደግሞም መሀል ለመሀል ሆኖ በአረንጓዴ ሱፍ ክር ላይ የተሰፋውን ተረተሩት፡፡ በአጭር መሸርገጊያ የተዘጋ ባለ ክዳን ኪስ ሆኖ ውስጡ በላስቲክ የተጠረዘ ነው፡፡ የቡና፣ የአቢሲኒያና፣ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የገንዘብ ማስቀመጫ ደብተሮች ናቸው በውስጡ የተገኙት፡፡ ከቡና ባንክ ብር184,000፣ ከአቢሲኒያ ባንክ ብር79,000፣ ከኢትዮጵያን ንግድ ባንክ ሰባት መቶ አርባ ሺህ ብር ይላሉ ፡፡

ከላይ ከተገኙት የአራት ብድር ስምምነት ሰነዶች ከሁለት የታወቁ ነጋዴዎች የመኪና ሊብሬና የቤት ፕላን ካርታ ዋስትና የተሰጠ ነዉ፡፡ ብር631,500 በመረጃ በእዝግቢት መያዙ በነባሪዎች ፊት ተፅፎና ተፈራረሙውበት ጣቢያ አዛዥ ዋና ኢንስፔክተር ይግዛው ታሪኩ ታዛቢዎች ባሉበት ጥሬ ገንዘብ በጊዜያዊነት በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ እንዲቀመጥ ተወሰነ፡፡

በበረንዳዉ የተሰባሰበው ሰው ጉድ አለ፡፡ ከፊሉ ይራገማል፡፡ ከፊሉ ከእንግዲህ አፍ አውጥቶ ለሚለምን አምስት ሳንቲም ላልሰጥ……ይምላል፣ ይገዘታል፡፡

ከሞጣ መጥቶ ባህር ዳር ኗሪ የሆነው ለምኖ አዳሪ አዛናው ይልቃል ግን እስካሁን በሱ ላይ ምን ትዝብት እንደተፈጠረ አላወቁም፡፡ ጉዳቱ ከባጃጇ ተሳፍሮ ወደ ማደሪያው ሽንብጥ ቀበሌ ጋሪ ሰፈር ሊያመራ ሲል ነበር በጫፍ በኩል እንዳለ በግጭቱ ግፊት ተሰፈንጥሮ እንደወደቀ ከአሣ ኮርፖሬሽኑ ፊት ለፊት የአስፓልቱ ጠርዝ የአትክልት አጥር ብረት ላይ ተጋጭቶና ወድቆ ጭንቅላቱ ተበርቅሶ ብዙ ደም ፈሶትና ጀርባው ላይ ደቅቆ ተመትቶ በአንሳ አንሳ ተነስቶ ወደ ሆሲፒታሉ የገባው፡፡

ወ/ሮ ዘውዴ አንዳሳ ጊዮርጊስ ከተዋወቋት ቀበሌ 13 ቆዳ ሰሪዎች ሰፈር ከምትኖረው መነኩሴ ለምኖ አዳሪ ቤት ለመሄድ ነበር የተሳፈሩት ብዙ ደም ፈሷቸዋል፡፡ ከድንጋጤው ጋር ተደማምሮ ራሳቸውን ረስተዋል፡፡ አንዴ ብቻ ቀዶ ህክምና ክፍሉ እያሉ ከረጢቱ ከአንገታቸው ሲፈታና ሻንጣው ሲወልቅ ባትተው ነበር፡፡ ከዚያ በኋላ አልነቁም፡፡ የወ/ሮ ዘውዴ ከረጢት ሲወልቅ በመዘቅዘቁ ብሮች ወረቀቶችና ሳንቲሞች ተዘርግፈው ስለነበር የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር አስተዳደሩና ፖሊስ ባለቤት ተቆጥሮና ተመዝግቦ ተቆጥሮ ደብተሮችም ተነበው በአደራ ወ/ሮ በለጡ ፊርማ ተረክባው አደረች፡፡

ሹፌሩ ጉዳቱ ለሕይወቱ ቢያሰጋውም ቀኝ እግሩና ታፋው ተቀጥቅጧል፡፡ እማ ዘዉዴ ከማደንዘዣው በኋላ የማህፀን ህመማቸው ፈሳሽ ጨምሮባቸዋል፡፡ ከላይ ከላይ ይተነፍሳሉ፡፡ አናታቸው በመታከሙ ከማጅራታቸው ስር መደገፊያ ተደርጎላቸው በጀርባቸው ተኝተዋል አልፎ አልፎ ቅዥት ያሰማሉ ሰው መለየት ግን አልቻሉም ከአዛናው አንፃር ሲታዩ የተሻሉ ቢመስሉም የህክምና ባለሙያዎች መሯሯጥ አስታማሚዎችን አስጨንቋል ፡፡

የየኳሳው አስናቀ ጉዳት ቀላል እንደሆነ ስለተነገረው ተረጋግቷል፡፡ የአልማዝ ተመላልሳ መጠየቋና ለችግሩ መድረሷ አስደስቶታል የሳህኑና የፔርሙሱ አይነትም ልዩ ሀብታም አስመስሎታል ፡፡

የህፃናቱ ጉዳት ቀላል በመሆኑ በተደረገላቸው እርዳታ ደህንነታቸው ተረጋግጧል፡፡ አራት ሰአት ላይም ወደ መጡበት እንዲሄዱ ተነግሯቸዋል፡፡ ነርሷ ግን ታሪካቸውን ስላወቀች ምሳ በልተው እንዲሄዱ ፈቅዳለች፡፡

የአዘናው ይልቃልና የእማ ዘውዴ ታሪክ በሆስፒታሉ ሀኪሞችና ሠራተኞች አስታማሚዎችና ታካሚዎች ዘንድ ከመኝታ ክፍል ወደ መኝታ ክፍልና በተመላልሶ ታካሚዎች፣ በሶስተኛ ፖሊስ ጣቢያና በመምሪያው ፖሊሶች ሳይቀር በመወራቱ ጉድ ተብሏል፡፡ በታክሲና ባጃጅ ሠራተኞች በኩል ወሬው በከተማው እየተወራ ነው፡፡

የልመናን አስከፊነትና አዋራጅነት የተረዱ ወገኖች ያሉትን ያክል ነገሩን ሳያገናዝቡ «ታዲያ ምን ይስሩ? በገዛ ሀገራቸው የመለመን መብት የላቸውም እንዴ?» የሚሉ የዋህ አዛኞች አይታጡም፡፡ «በፈጣሪ ስም ከለመነ የፈለገ ይክበርበት ምፅዋት አይከለከልም፡፡ የእምነት አባቶች መስጠት ፅድቅ ነው ብለዋል፡፡» የሚሉ ሳይገባቸው እንደገባቸው ሆነው ልመናንና ጥገኝነትን የሚያበረታቱም ይሰማሉ፡፡

ብዙው የህብረተሰቡ ክፍል ግን መስራትና መለወጥ የማይችሉ የከፋ የጤና ችግር ያለባቸውን፣ ከዋኝ ጧሪና ተንከባካቢ የሌላቸውን አረጋውያን፣ ለመኖር የከፋ ችግር ያለባቸውን አካል ጉዳተኞች፣ ተስፋና ጥግ ያጡ ህፃናትን፣ በድንገተኛ አደጋና ችግር የተፈናቀሉ ወገኖችን ሲያይ አንጀቱ አይችልም፡፡ ኪሱንም ሆነ ፖርሣውን ……የአቅሙን ይለግሣል፡፡

ከባህር ዳ ርከተማ፣ ከስማዳ፣ ከጎንደርና ከአዲስ አበባ የመጡ የቁስለኞች ቤተአዝማዶችና የእማ ዘውዴ የዶክተሩ ልጃቸው ባለቤት ምራታቸው በጭንቀት ተውጠዋል፡፡ «ግን መቼ መጥታ ነው ከጠበሉ? ጠበል መቆየቷን ሰምቼ ውጤት ካላገኘሽበት ወደኔ ነይ በሕክምና ይሞከርልሽ ብያት ነበር እኮ!» አለች ምራታቸው ሲስተር ሲቲና፡፡

«እረተይኝ እቴ ካንሰር ከሆነ ችግሯ ቆይቷል፡፡ ግን በጠበሉ ተስፋ አገኘሁ ስትል ነበር ቤቷን ጥላ ስትንከራተተት የቆየችው አለች፡፡ በቤታቸው ያሳደጓት የትልቅ እህታቸው ልጅ፣ የጤና መኮንኗ ወ/ሮ በለጡ ቀጠለችና ሚስጢሩ ጠበል ብላ ከሄደች በኋላም በልመና አዳር ቀጠለችበት፡፡ ይኸውልሽ! ወደ ቀዶ ህክምና ክፍል ስትገባ ከአንገቷ የተገኘው ከረጢትና አንግታው የነበረው ሻንጣ ውስጥ ብር 13,271.47 ነዉ የተገኘው፡፡ ፖሊሶች ብሩን ቆጠረው በፊርማ ለኔ በአደራ ከሰጠኝ በኋላ ነው እኛ ባለንበት የሚሆነው ይሆናል ብለው የሄዱትና ረፋዱ በንግድ ባንክ ሒሳብ ቁጥር ገቢ የተደረገዉ፡፡ የሚገርመዉ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ደብተሯም እኮ 234,563.69 ይዞ ተገኝቷል፡፡ እንግዲህ ቤቷን፣ የንግድ ድርጅቷን መቁረጫ ልጇ የሚያስተዳድረውን ሱቅና ወፍጮ ከአምስት አመት ወዲህ የመጣ ክብረት ተመልከች!፡፡ አንች ብቻ ነሽ እንጂ ያልሰማሽ ከዚህ ያለው ሁሉ ሰምቶ አፍሮ ቢመክራት አልሰማ ብትል ተስፋ ቆርጦ ትቶት ነው፡፡ ዛሬ ብትሞት እንኳ ዋይ ብሎ ለማልቀስ እኔ እንኳ ያሳፍራል አለች፡፡ ደገመችና፡፡

እንኳን ባለቤቱ ቀድሞ ሞተ ወይ አፈር በበላሁት አለች ምራታቸው ሲስተር ሲቲና፡፡ የወሮ በለጡን አይን ትክ ብላ እያየች፡፡ ድንገት ጩኸት ተሰማ፡፡ የሆስፒታሉ ሠራተኞች «በቃ ዝምበሉ፣ ውጭ ታለቅሳላችሁ»! እያሉ ለቅሶውን ለማስቆም ሞከሩ፡፡ አስታማሚውና የቁስለኛው ታላቅ ወንድም የወንድሙ በልመና ቤቱን ትቶና ወጥቶ በማይወደው የመመፅወት ኑሮ ተሰልፎ መሞቱ ቢያናድደውም የሆስፒታሉን የአልጋና የህክምና ቀሪ ገንዘብ ከፍሎ አስክሬኑን ይዞ ሲወጣ ብዙ ሰው አጅቦት እስከ በሩ ድረስ ሸኘው፡፡

የእማ ዘውዴ አስታማሚ «በለጥዮ መድሀኒት ግዙ ተብሏል» አለች ሮጥ ብላ መጥታ ሲስተር ሲቲና ከግቢው መድሀኒት ቤት ስለሌለ ከተማ ግዙ የተባለውን የመድሀኒት ማዘዣ ይዛ ከወ/ሮ በለጡ ጋር ታክሲ ይዘው ወደ ከተማ ጉዞ ጀምረዋል፡፡

ታክሲ ውስጥ ከአሮጊቷ ቁስለኛም ሆነ ከሞጣ መጥቶ በባህር ዳር ከሚለምነው ለማኝ የተገኘውን ገንዘብ መጠን በማዳነቅ እያወሩ ሲጓዙ አንዷ አንስታ «ሺህ አመት አይኖር! ዘውዴ ያሏት ለማኝ ቁስለኛ ደግሞ ሰፊ ሀብት ያላት ናት፡፡ ከዚያም በላይ እንዳላወቀ የሚያኖር የግሉ ትልቅ የህክምና ተቋም ያለው ልጅ ያላት ናት፡፡ የሚገርም እኮ ነው የተገኘባት የብር መጠን» ስትል በአደንቁልኝ አወራች፡፡

ሌላዋም ተቀብላ «እህቷና የእህቷ ልጅ የሞተች መስሏቸው ተጠርተው መጥተዋል፡፡ እነርሱ ራሳቸው ሥጋ ሆናባቸው ነው እንጂ ያዩትና የሰሙት ነገር አስገርማቸዋል፣ አሳፍሯቸዋልም“፡፡ አለች ድምፃን ጎላ አድርጋ፡፡ «አይ ልመና! ምን ያርጉ? ጥፋቱ የኛው ነው፡፡» አስተዉለንና የተቸገረውን መርጠን

> ደረቶው ሲነሳ ከብዷል በቁርጥ በቁርጥ በአራት ድራብ ጨርቅ በሁለት ገፅ የፕላስቲክ ሸራ፣ በመሀል፣ አብጄዲ ጨርቅና መልሶ ፕላስቲክና እራፊ ጨርቆች ተጀብኖ በዝሃና በሲር ክር በጥንቃቄ በየስንዝሩ ርቀት በአራት ማዕዘን የተሰፋ ነዉ፡፡

አንሰጥም ?ምን ያድርጉ? እነርሱ.... «እየተባለ ወሬው ደርቷል፡፡ ሁለቱም በአይን ተግባብተው እናት መድሀኒት ቤት ሲደርሱ ወረዱ፡፡

ሰማሽ ጉዳችንን አለች ወ/ሮ በለጡ ወደ ሲስተር ሲቲና ፊቷን አዙራ «በቃ ትትረፍ እንጂ በባለቤቷና በወንድሞቿ ይዘን አስምለን እናስቆማታለን፡፡» አለች ሲስተር ሲቲና መድሀኒቱን ገዝተው ወደ ሆስፒታል እየተመለሱ፡፡ «ሀኪሙ ተመልሶ መጥቶ ቤት ወስዳችሁ አስታሙ» ብሏል አለች አስታማሚዋ ቀድማ፡፡ «እንዴት ቅድም መድሀኒት ግዙ ብሎ አልነበረም እንዴ? ሲስተር ሲቲና ጠየቀች፡፡ አይ ከሌሎች ሀኪሞች

ወደ ገጽ 14 ዞሯል

# Photo Gallery



*The 11th Nations, Nationalities and Peoples day celebration at BDU*



















*International Day of people with disability at BDU*